# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ሰኞ 83ኛ ዓመት ቁጥር 294 ሰኔ 24 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




ፎቶ፦ ዳኜ አበራ

## ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)

ከአፍሪካ ታላላቅ የቀድሞ የእግር ኳስ ተጫዋቾች ጋር ትናንት የወዳጅነት እግር ኳስ ጨዋታ አካሂደዋል። ከጨዋታው መጠናቀቅ በኋላ ናይጀሪያውያኑ ንዋንኮ ካኑና ዳንኤል አሞካቺ፣ ሴኔጋላዊው ሄንሪ ካማራ እንዲሁም የተለያዩ የቀድሞ የእግር ኳስ ተጫዋቾች በወዳጅነት ፓርክ ቁጥር 2 ጊቢ ከጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ጋር የአረንጓዴ ዐሻራ መርሃ ግብር አከናውነዋል።

# ከመኸር እርሻ 616 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ለማግኘት እየተሠራ ነው

- ከአራት ሚሊዮን ሄክታር በላይ መሬት በአዝርዕቶች ተሸፍኗል
- 14 ሚሊዮን ኩንታል የአፈር ማዳበሪያ እየተሠራጨ ነው

ታደሠ ብናልፈው

አዲስ አበባ፡- በ2016/17 ከመኸር እርሻ 616 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ለማግኘት የማሳ ዝግጅት እየተደረገ ነው ሲል የግብርና ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡ 14 ሚሊዮን ኩንታል የአፈር ማዳበሪያ ወደ ሀገር ወስጥ ገብቶ ለአርሶ አደሩ እየተሠራጨ መሆኑም ተጠቁሟል፡፡

የግብርና ሚኒስቴር የሕዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ሥራ አስፈፃሚ አቶ ከበደ ላቀው ለኢፕድ እንደገለጹት፤ በ2016/17 በመኸር እርሻ 20 ነጥብ አራት ሚሊዮን ሄክታር መሬት በሰብል ዘር በመሸፈን 616 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ለማግኘት የማሳ ዝግጅትና ግብዓት የማቅረብ ሥራ እየተሠራ ነው፡፡

በሀገሪቱ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ በዓመት

ከመኸር እርሻ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል














## የኢኮኖሚ

### ልዩ ዞን ሥርዓት ለኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ያለው ፋይዳ

ዳግማዊት አበበ

ዜና ትንታኔ

በኢትዮጵያ የኢንዱስትሪ ፓርኮችን ወደ ልዩ የኢኮኖሚ ዞን ሥርዓት በማሸጋገር የሀገሪቱን ኢኮኖሚያዊ እድገት ለማፋጠን ከሰሞኑ

የኢኮኖሚ ልዩ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



## በቡታጅራ ከተማ

### በቀን ከ23 ሺህ ሊትር በላይ ወተት ለገበያ እየቀረበ ነው

ገጽ 4






አቶ ደስታ ለገሰ

# በክልሉ የክረምት በጎ ፈቃድ ስምንት ሚሊዮን ችግኝ ስመትከል ታቅዷል

- 800 አዳዲስ ቤቶችን የመገንባት ሥራ ተጀምሯል
- አንድ ሺህ 200 ቤቶች እድሳት ይደረግላቸዋል

**ዮርዳኖስ ፍቅሩ**

አዲስ አበባ፡- የሲዳማ ክልል በያዝነው ዓመት የክረምት በጎ ፈቃድ አገልግሎት ስምንት ሚሊዮን ችግኞችን ለመትከል ማቀዱን አስታወቀ፡፡

በክልሉ የሴቶች ወጣቶችና ማኅበራዊ ጉዳይ ቢሮ ምክትል ኃላፊ አቶ ደስታ ለገሰ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳስታወቁት፣ ክልሉ በተያዘው ዓመት ለሚደረግ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት የክልሉ ፕሬዚዳንትን ጨምሮ የዞንና የወረዳ የየዘርፍ አመራሮች በተገኙበት ማስጀመሪያ መርሀ ግብር አካሂዷል፡፡

በየዞኑ ያሉ ቢሮዎችም እያንዳንዳቸው ምን ምን ተግባራትን እንደሚያከናውኑ የየድርሻቸውን ወስደዋል፡፡

በክልሉ በ2016 የክረምት በጎ ፈቃድ አገልግሎት ስምንት ሚሊዮን ችግኞችን ለመትከል የታቀደ ሲሆን፣ 800 አዳዲስ ቤቶችን ሠርቶ ለአቅመ ደካሞች ለማስረከብ ሥራዎች ተጀምረዋል፡፡

ኃላፊው እንዳስታወቁት አዳዲስ ከሚሠሩት ቤቶች በተጨማሪ አንድ ሺህ 200 የአቅመ ደካማ ቤቶችም እድሳት የሚደረግላቸው ይሆናል፡፡

ቤቶችን ከመስራትና ከማደስ በተጨማሪ አነስተኛ ጓሮ ላላቸው ሰዎች እንሰት የመትከል ሥራም የሚሠራ መሆኑን ጠቅሰው፤ በተያዘው ዓመት የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ከዚህ ቀደም ከሚደረገው በተለየ ችግኝ ከመትከል ባሻገር ለመብል የሚሆኑ አትክልቶችና ፍራፍሬዎችን የመትከል ተግባርም ይከናወናል፡፡

አቶ ደስታ እንደተናገሩት፣ በዘንድሮው የክረምት የበጎ ፈቃድ አገልግሎት በክልሉ በአጠቃላይ ከ61 ሺህ በላይ ወጣቶች በ13 የተለያዩ የአገልግሎት ዘርፎች የሚሳተፉ ይሆናል፡፡

ከችግኝ ተከላና ከቤት እድሳት በተጨማሪ፣ የደም ልገሳ፣ ድጋፍ ለሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎች ማገዝ፣ ሰላምና ፀጥታን ማስከበር፣ ተላላፊ በሆኑና በሌሎችም በሽታዎች ላይ ህብረተሰቡን ግንዛቤ ማስጨበጥ፣ የመንገድና ትራንስፖርት ደድህንነት፣ የመንገድና ሌሎችም መሠረተ ልማቶች ጥገና እና ጽዳት ወጣቶቹ ከሚሳተፉባቸው የበጎ ፈቃድ አገልግሎቶች መካከል ይገኙበታል፡፡

ጎጂ ልማዳዊ ደርጊቶችን ለማስቀረትና በክልሉ ብዙም ባይታይም ሕገ ወጥ የሰዎች ዝውውርና ከገጠር ወደ ከተማ የሚደረገውን የሰዎች ፍልሰት ለመከላከልም እንዲሁ የግንዛቤ ማስጨበጥ ሥራዎች በወጣቶቹ አማካኝነት ይከናወናሉ፡፡

በክረምቱ መርሃ ግብር በሚከናወኑ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት በአጠቃላይ ከአንድ ሚሊዮን 600 ሺህ በላይ ሕዝብን ተጠቃሚ ለማድረግ የታሰበ ሲሆን፣ በዚህም ከ749 ሚሊዮን በላይ ከሕዝብና ከመንግሥት ይወጣ የነበረን ብር ለማስቀረት ታቅዷል፡፡

ወጣቱ በክረምት ወራቱን በእረፍት የሚያሳልፍ መሆኑን አንስተው ይህንን የእረፍት ጊዜ አልባሌ ቦታዎች ላይ ከማሳለፍ ይልቅ ነገ ለመጪው ትውልድ ምሳሌና አርዓያ በሆኑ ተግባራት ላይ በመሳተፍ ህብረተሰቡን እንዲያገለግል ጥሪ አስተላልፈዋል፡፡

# አውደ ርዕዩ የትራንስፖርት ዘርፉን የኢንቨስትመንት ዕድሎች ለማስተዋወቅ ያግዛል

- የአውቶሞቲቭ ትራንስፖርት አውደ ርዕይ ከሰኔ 26 ጀምሮ ይካሄዳል

**መስከረም ሰይፉ**



አዲስ አበባ፡- በቀጣይ ሳምንት የሚካሄደው የአውቶሞቲቭ አውደ ርዕይ በትራንስፖርት ዘርፍ የሚገኙ የኢንቨስትመንት ዕድሎችን ለማስተዋወቅ ምቹ አጋጣሚ እንደሚሆን የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

ሚኒስቴሩ ከኢትዮ አውቶ ቴክ ትሬዲንግ ጋር በመተባበር በትራንስፖርት፣ ሎጂስቲክስና በአቶሞቲቭ ኢንዱስትሪ ላይ ያተኮረ አውደ ርዕይና የፓናል ውይይት ከሰኔ 26-28 ቀን 2016 ዓ.ም እንደሚያካሂድ አመላክቷል።

የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር የሕዝብ ግንኙነትና የኮሙኒኬሽን ሥራ አስፈጻሚ አመለወርቅ ህዝቅኤል በወቅቱ እንደገለጹት ፤ አውደ ርዕዩ በትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ዘርፍ እየተሠሩ ያሉ ሥራዎችንና ቴክኖሎጂዎችን ለማስተዋወቅ እንዲሁም የዘርፉን ባለድርሻ አካላት ለማስተሳሰር ያለመ ነው፡፡

በትራንስፖርት ዘርፉ በርካታ መሻሻሎች መምጣታቸውን ጠቁመው፤ አውደ ርዕዩ በተለይም በአሁኑ ወቅት ወደ ኢትዮጵያ እየገቡ የሚገኙ የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎችን እንዲሁም በትራንስፖርት ዘርፉ ለመሠማራት የሚረዱ አስቻይ ሁኔታዎች ለማስተዋወቅና በዘርፉ የተሠማሩ አካላትን በማበረታታት ትልቅ ሚና እንደሚኖረው አብራርተዋል፡፡

በአውደ ርዕዩ የፓናል ውይይት እንደሚካሄድ ገልጸው፤ በዘርፉ ያሉ ማነቆዎችን ለመለየትና መፍትሄ ለመስጠት የሚያግዝ ግብዓት እንደሚገኝበት አመላክተዋል።

በትራንስፖርት ዘርፉ ለመሠማራት በተለይም የውጭ ዜጋዎች መጀመሪያ የሚጠይቁት ጉዳይ የትራንስፖርት ደህንነቱን በተመለከተ መሆኑን አንስተው፤ በአውደ ርዕዩ አስተማማኝና ደህንነቱ የተጠበቀ የትራንስፖርት አገልግሎት ተደራሽ ለማድረግ እየተሠሩ ያሉ ሥራዎች ይተዋወቃሉ ብለዋል፡፡

የትራንስፖርት ፖሊሲ ፣ ስትራቴጂዎች እንዲሁም ቀጣይ አቅጣጫዎች ላይ ያተኮሩ ውይይቶች እንደሚካሄዱም አስረድተዋል።

በአውደ ርዕዩ 150 ተሳታፊዎችና አምራች ኩባንያዎች እንደሚሳተፉ ጠቁመው፤ ለኩባንያዎቹ የገበያ ትስስር በመፍጠር የአውቶሞቲቭ ኢንዱስትሪውን የሚያነቃቃ ሥራ እንደሚከናወን ተናግረዋል።

የኢትዮ አውቶ ቴክ ትሬዲንግ ሥራ አስኪያጅ አዲስ አለማየሁ (ኢ/ር) በበኩላቸው በአውደ ርዕዩ አዳዲስ ቶክኖሎጂ ይዘው የሚመጡ ተቋማት መኖራቸውን አመላክተው፤ ተቋማቱ ምርታቸውን የሚያስተዋውቁበት ሰፊ ዕድል እንደሚፈጠር ገልጸዋል።

በአውደ ርዕዩ የተለያዩ የተሽከርካሪ አይነቶች ለእይታ እንደሚቀርቡ ጠቁመው፤ በተጨማሪ ለታሳታፊዎች ከመንገድ ደህንነት ጋር በተያያዘም ግንዛቤ የማስጨበጫ መርሀ ግብሮች እንደሚከናወኑ አስረድተዋል።

በፓናል ውይይቱ ላይ ደግሞ በዘርፉ ላይ የሚነሱ በርካታ ችግሮችና የመፍትሄ ሃሳቦች ላይ ምክክር እንደሚደረግ አስታውቀዋል።



# ኢትዮጵያ ከማዕድን ሀብቷ ተገቢውን ጥቅም እንድታገኝ እየተሠራ ነው

**ማህሌት ብዙነህ**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ ካላት የማዕድን ሀብት ተገቢውን ጥቅም እንድታገኝ እየተሠራ መሆኑን የማዕድን ሚኒስቴር አስታወቀ።

የዓለም የከበሩ ማዕድናት ማህበር በሀገሪቱ ለመጀመሪያ ጊዜ በከበሩ ማዕድናት ዘርፍ ያሠለጠናቸውን ተማሪዎች አስመርቋል።

የማዕድን ሚኒስትር ኢንጂነር ሀብታሙ ተገኝ በወቅቱ እንደገለፁት፤ ኢትዮጵያ ካላት የማዕድን ሀብት ተገቢውን ጥቅም እንድታገኝ በትኩረት እየተሠራ ነው። በዘርፉ የተመረቁት ተማሪዎችም ሀገሪቱ በማዕድን ዘርፍ የሚገባትን ጥቅም እንድታገኝ ጉልህ ሚና ይጫወታሉ።

ተመራቂዎች ኢትዮጵያ ከከበሩ ማዕድናት ዘርፍ የሚገባትን ጥቅም እንድታገኝ በማድረግ ወደ ቀጣይ ምዕራፍ ለማሸጋገር የሚያስችሉ መሆናቸውን ጠቅሰዋል።

ኢትዮጵያ በርካታ ማዕድናት ያሏት ቢሆንም በዘርፉ የሠለጠነ የሰው ሀብት ባለመኖሩ ያሏትን ሀብቶች በቅጡ የማወቅና የመጠቀም ክፍተት አለ ብለዋል።

የሀገር ውስጥ ባለሙያ ባለመኖሩም ማዕድናትን እሴት ሳይጨመርባቸው በጥሬው በመላክ በሚፈለገው ልክ የውጭ ምንዛሪ ማግኘት እንዳይቻል ሆኗል ብለዋል።

በመሆኑም በዘርፉ እውቅና ያላቸው ባለሙያዎች አስፈላጊ በመሆኑ የዓለም የከበሩ ማዕድናት ማህበር ለ 11 ወራት ያሠለጠናቸውን 12 ባለሙያዎች ማስመረቅ ችሏል።

ይህም ኢትዮጵያ በዘርፉ ያላትን ሀብት በማወቅና ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ ማዕድናት እሴት በመጨመር ለዓለም ገበያ ተወዳዳሪ ምርት በማቅረብ መገኘት የሚገባው ጥቅም እንዲገኝ የሚያስችል መሆኑን አስታውቀዋል።

ተመራቂዎቹም ዘርፉን ወደ ተሻለ ደረጃ በማሳደግ ኢትዮጵያ ለዓለም ገበያ ተወዳዳሪ የሆኑ የከበሩ ማዕድናትን እንድታቀርብ ሃላፊነት ተጥሎባቸዋል ሲሉ ገልጸዋል። በዘርፉ ለሚሠማሩ ባለድርሻ አካላትም ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ አስፈላጊውን ድጋፍ አጠናክሮ ይቀጥላል ሲሉ ተናግረዋል።

የዓለም የከበሩ ማዕድናት ማህበር መሥራችና ሊቀመንበር ሚስተር ጆፍሪ ዶሚኒ በበኩላቸው፤ ኢትዮጵያ በአፍሪካ የከበሩ ማዕድናት በስፋት ከሚገኙባት ሀገራት ውስጥ አንዷ መሆኗን ጠቅሰው፤ ሥልጠናውም በዘርፉ የሠለጠነ የሰው ሀብት በማፍራት ሀገሪቱ ያላትን የማዕድን ሀብት በአግባቡ ለመጠቀም የሚያስችል ነው ብለዋል።

ኢትዮጵያ ያላትን የማዕድን ሀብት በአግባቡ ለመጠቀም መጀመሪያ በዘርፉ ብቁ የሰው ኃይል ማፍራት ይገባል ያሉት ደግሞ በዓለም የከበሩ ማዕድናት ማህበር የአፍሪካ ዳይሬክተር ወይዘሪት ሃይማኖት ሲሳይ ናቸው። ለዚህም ማህበራቸው በኢትዮጵያ በከበሩ ማዕድናት ላይ እሴት መጨመር የሚችሉ የሰው ሃይልን በማፍራት ላይ ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ መሆኑን ገልጸዋል።

ማህበሩ ባለፉት 11 ወራትም በምስራቅ አፍሪካ የመጀመሪያ የሆኑትን 12 የጂሞሎጂስት ባለሙያዎችን አሠልጥኖ አስመርቋል። እነዚህም ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪና ብቁ ባለሙያዎችን በማቅረብ ሀገሪቱ በዘርፉ ማግኘት የሚገባትን ጥቅም እንድታገኝ ያስችላል ብለዋል።

# የኮሪደር ልማቱ የመዲናዋን የትራፊክ ፍሰት ችግር ይፈታል

**ታደሠ ብናልፈው**

አዲስ አበባ፡- የኮሪደር ልማቱ በመዲናዋ የሚስተዋለውን የትራፊክ ፍሰት ችግር በመፍታት የተሻለ የትራፊክ እንቅስቃሴ እንዲኖር የሚያስችል ነው ሲል የአዲስ አበባ ከተማ ትራፊክ አስተዳደር ባለሥልጣን አስታወቀ፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትራፊክ አስተዳደር ባለሥልጣን የትራፊክ የመንገድ ትራፊክ ደንብ ማስከበርና ቁጥጥር ዳይሬክተር አቶ አያሌው አቲሳ ለኢፕድ እንደገለጹት፤ እየተገነባ ያለው የኮሪደር ልማት የተሽከርካሪዎችን መንገድ የሚያሰፋ፣ እግረኞችን መንገድ የለየና እንደልብ እንዲቀሳቀሱ የሚያስችል በመሆኑ በመዲናዋ የሚስተዋለውን የትራፊክ ፍሰት ችግር ፈትቶ የተሻለ የትራፊክ እንቅስቃሴ እንዲኖር የሚያስችል ነው፡፡

በመዲናዋ እየተሠራ ያለው የኮሪደር ልማት ሰፊና እግረኞችን እንደልብ የሚያቀሳቅስ፣ የብስክሌት መንገድ ያለውና ዜጎች አማራጭ ትራንስፖርት እንዲጠቀሙ የሚያስችል መሆኑን ጠቅሰው፤ የተሽከርካሪዎችን መንገድ የሚያሰፋ በመሆኑ የተሻለ የትራፊክ ፍሰት እንዲኖር የሚያደርግ ነው ብለዋል፡፡

የኮሪደር ልማቱ የትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡ የተሽከርካሪዎች መቆሚያ፣ ማውረጃና መጫኛ ቦታዎች ከዋናው መስመር ተለይተው ለብቻ ገባ ብለው እንዲገነቡ ያካተተ ነው ያሉት ዳይሬክተሩ፤ ይህም የመዲናዋን የትራፊክ ፍሰት ጤናማና ደህንነቱ የተጠበቀ በማድረግ በትራፊክ አደጋ የሚደርሰውን የሕይወትና የንብረት ውድመት የሚቀንስ ነው ሲሉ ገልጸዋል፡፡

የኮሪደር ልማት ከመጀመሩ በፊት በቂ የሆነ የእግረኛ መንገድ አልነበረም፤ በቂ የሆነ እግረኛ መንገድ አለመኖሩን ጠቅሰው፤ እግረኞች የተሽከርካሪ መንገድን ለመጠቀም ይገደዱ እንደነበር አንስተዋል፡፡

በዚህም ከ80 በመቶ በላይ የትራፊክ አደጋ ጉዳት እንዲደርስ መሆኑን ጠቅመው፤ የተሽከርካሪ መንገዶችም ጠባብ በመሆናቸው በሥራ መውጫና መግቢያ ሰዓት የትራፊክ መጨናነቅ መከሰቱን ተናግረዋል፡፡

የሰው ሕይወትና የንብረት ውድመት ይፈጠራል፣ የኮሪደር ልማቱ በትራፊክ ፈሰት የመጨናነቅ ችግር፣ በእግረኞች የመንገድ አጠቃቀም ሃላፊነት ጉድለት የሚከሰቱ የትራፊክ አደጋዎችን ይቀንሳል፡፡

የኮሪደር ልማቱ አማራጭ መንገዶችና የትራንፖርት አገልግሎት መፍጠር የሚያስችል በመሆኑ የትራፊክ ፍሰቱ ጤናማ፣ ደህንነቱ የተጠበቀ የሚያደርግ ነው ሲሉ ገልጸዋል፡፡

የኮሪደር ልማቱ ተጠናቆ አገልግሎት ሙሉ ለሙሉ መስጠት ሲጀምር የትራፊክ ፍሰቱን የተሳለጠ ከመሆኑም ባሻገር በሰውና በንብረት ላይ የሚደርስ አደጋ የሚቀንስ ይሆናል ሲሉ ተናግረዋል፡፡



አቶ አያሌው አቲሳ

ባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ በኮሪደር ልማት ሥራ የትራፊክ መጨናነቅ ችግር እንዳይከሰት፣ የአካል፣ የሕይወት፣ የንብረት ውድመት እንዳይከሰት በትኩረት እየሰራ ነው ያሉት ዳይሬተሩ፤ እየተሠራ ያለው ሥራ የኮሪደር ልማቱ እስከሚጠናቀቅ ተጠናክሮ ይቀጥላል ብለዋል፡፡



# ጠንካራ የሥራ ባህል ለመገንባትና የሀገርን ዕድገት ለማረጋገጥ የሴቶች ሚና ከፍተኛ ነው

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ፡- ጠንካራ የሥራ ባህል ለመገንባትና የሀገርን ዕድገት ለማረጋገጥ የሴቶች ሚና ከፍተኛ ነው ሲሉ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ ገለጹ።

"የተመራጭ ሴቶች ሚና ለሀገረ መንግሥት ግንባታ" በሚል መሪ ሃሳብ ከተማ አቀፍ የሴቶች የንቅናቄ ማስጀመሪያ መርሃ-ግብር ተካሂዷል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ በወቅቱ እንደገለጹት፤ ጠንካራ የሥራ ባህል ለመገንባትና የሀገርን ዕድገት ለማረጋገጥ የሴቶች ሚና ከፍተኛ ነው።

በከተማው የተገኘው የፕሮጀክት አፈጻጸም ውጤቶች በጋራ ትጋት የተገኙ ናቸው ያሉት ከንቲባ አዳነች፤ ዘላቂ ልማት ሊረጋገጥ የሚችለው ሁሉም በትብብር ሲሠራ መሆኑን ጠቁመዋል።

እንደ ከንቲባ አዳነች ገለጻ፤ በከተማው እየተከናወነ ያለው የኮሪደር ልማት እንዲሁም የሌሎች ፕሮጀክቶች አፈጻጸም ውጤታማነት ያለእረፍት መሥራት የቻሉ ጠንካራ ሴቶች ከንድ ጭምር ውጤት ነው። ለሀገር ሁለንተናዊ እድገት ጠንክሮ መሥራትና ሴቶች ላይ ያሉ ተለምዷዊ ተቅጽላዎች ለማስወገድ ሴቶች ግንባር ቀደም መሆን አለባቸው።

መሪነት ማለት ማስተባበርና አቅጣጫ መጠቆም ነው ያሉት ከንቲባዋ፤ የሚፈለገው ውጤት መምጣት የሚችለው ግን በበርካቶች የጋራ ትጋት መሆኑን አስረድተዋል።

በከተማዋ የተለያዩ የለውጥ ሥራዎች ቢከናወኑም አሁንም ያልተመለሱ በርካታ የሕዝብ ጥያቄዎች መኖራቸውን ጠቅሰው፤ በቀጣይም ያሉ ጥያቄዎችን በመመለስ ለትውልድ የእድገትና የብልጽግና በር እየከፈቱ መጓዝ እንደሚያስፈልግ አብራርተዋል።

የአዲስ አበባ ምክር ቤት ዋና አፈጉባኤ ወይዘሮ ቡዜና አልቃድር በበኩላቸው፤ የሕዝብ ተመራጭ ሴቶች በሀገረ መንግሥት ግንባታ ላይ ያላቸው ሚና በግንባር ቀደምትነት መወጣት ይገባቸዋል ብለዋል።

ወይዘሮ ቡዜና አክለውም፤ ሴቶች ከተረጂነት በመውጣት እራሳቸውን እንዲችሉ እና እያደረጉ ተረጂነት በማስወገድ ምርታማነት ማረጋገጥ እንደሚያስፈልግ ተናግረዋል።

የንቅናቄው ዋና ዓላማ ሴት የምክር ቤት አባላትና አመራሮች በቅንጅት ሠርተው ውጤት ማምጣት እንዲችሉ መሆኑንም ነው ወይዘሮ ቡዜና የጠቆሙት።

በከተማው ከዚህ በፊት በተሠሩ ንቅናቄዎች አበረታች ውጤት ማስመዝገብ ተችሏል ያሉት ወይዘሮ ቡዜና፤ ለአብነትም የከተማ ግብርናው እንዲሁም የሌማት ትሩፋት ፕሮግራሞች መተግበራቸውን ጠቅሰዋል።

# "የኤሌክትሮኒክስና የገጽ ለገጽ ጥምር ማስተማሪያ ዘዴ የሥልጠና ጥራትና ተደራሽነት የሚያረጋግጥ ነው"

**- የቴክኒክና ሙያ አሠልጣኞች**

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ፡- በቴክኒክና ሙያ፣ ሥልጠና ተቋማት የተጀመረው የኤሌክትሮኒክስና የገጽ ለገጽ ማስተማሪ ዘዴ በቅንጅት መሠጠቱ የሥልጠና ጥራትና ተደራሽነት የሚያረጋግጥ መሆኑን የቴክኒክና ሙያ አሠልጣኞች ገለጹ።

ካለፉት አራት ዓመታት በፊት የቴክኒክና ሙያ፣ ሥልጠና በኤሌክትሮኒክስና ገጽ ለገጽ ማስተማሪ ዘዴ በቅንጅት ለመስጠት ሲተገበር የነበረው ፕሮጀክት በ15 ተቋማት ተግባራዊ እየተደረገ ይገኛል።

በቴክኒክና ሙያ፣ ሥልጠና ኢኒስቲትዩት የሊደርሺፕ ሥልጠና ማዕከል ዳይሬክተር፣ የፕሮግራሙ አባልና የኢንተርፕሪነርሺፕ ትምህርት ክፍል አሠልጣኝ ኤደን ከበደ ለኢፕድ እንደገለጹት፤ በተቋማቱ የተጀመረው የኤሌክትሮኒክስና የገጽ ለገጽ ማስተማሪ ዘዴ በቅንጅት መስጠት የሥልጠና ጥራትና ተደራሽነት የሚያረጋግጥ ነው።



አሠልጣኝ ኤደን ከበደ

በዘርፉ ውጤታማ ለመሆን ዓለም አቀፍ የትምህርት ሥልጠና የሚፈልገውን መስፈርት ማሟላት ያስፈልጋል ያሉት አሠልጣኝ ኤደን፤ ዓለም በፍጥነት እያደገች ከመሆኑ፣ የቴክኖሎጂ ውጤቶች ከመበራከታቸውና በፍጥነት የሚቀያየር በመሆኑ ከዓለም እኩል መራመድ የሚችል የሥልጠና ሥርዓት መገንባት አስፈላጊ ነው ብለዋል።



አሠልጣኝ ፍራዖል በቀለ

እንደ አሠልጣኝ ኤደን ገለጻ፤ ከዚህ በፊት በማንዋል የሚዘጋጅ የነበረውን በዲጂታል መልኩ ይዘቶች በማዘጋጀት ተማሪዎች ባሉበት ቦታ ሆነው መማር እንዲችሉ ምቹ ሁኔታ እየፈጠረ ይገኛል። በተጨማሪም ተግባር ተኮር በሆነና ሁሉንም አሳታፊ በሆነ መልኩ እየተሰጠ ነው።

በኢኒስቲትዩቱ ምቹ መሠረተ ልማት እንዲሁም ጠንካራ የኢንተርኔት አገልግሎት መኖሩንም ነው ያስረዱት።

የአርባምንጭ ሳተላይት ኮሌጅ አሠልጣኝ ፍራዖል በቀለ በበኩላቸው፤ የኤሌክትሮኒክስና የገጽ ለገጽ ማስተማሪ ዘዴ በቅንጅት መሠጠቱ ቦታ፣ ሰዓት እንዲሁም የሰው ኃይል እጥረት ሳይገድብ መስጠት ከመቻሉም በላይ ሠልጣኞች በንድፈ ሃሳብ የተማሩትን ከአሠልጣኞቻቸው ጋር በመገናኘት በተግባር ማየት የሚችሉበት መሆኑን ጠቁመዋል።



አሠልጣኝ ሙሉ አሰፋ

አሠልጣኝ ፍራዖል አክለውም፤ በፕሮጀክቱ የተለያዩ ሥልጠናዎችን ማግኘት ችለናል ያሉ ሲሆን መሠረተ ልማቶች ተሟልተው በሁሉም ተቋማት መጀመር ቢቻል በአጭር ጊዜ በዘርፉ የተያዘውን ግብ ማሳካት እንደሚቻል አብራርተዋል።

በአሠልጣኞችና ሠልጣኞች መካከል ያለውን ግንኙነት ከማሳደግ ጎን ለጎን በርካታ ወጣቶች ለቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ዘርፍ ዝንባሌ እንዲኖራቸው የሚያስችል ነው ያሉት ደግሞ የባህርዳር ሳተላይት ካምፓስ አሠልጣኝ ሙሉ አሰፋ ናቸው።

የሥልጠና ዘዴው ሠልጣኞች በቀላሉ የሥልጠና ግብዓት፣ መመዘኛ እንዲሁም መልመጃዎች እንዲያገኙ የሚያግዝ ነው ያሉት አሠልጣኝ ሙሉ፤ ቴክኖሎጂውን በመጠቀም ሠልጣኞች አዳዲስ የሆኑ ነገሮችን ባሉበት ቦታ ላይ እንዲገኙ ማስቻሉን ገልጸዋል።

ሥልጠናው በሁለቱ ማሠልጠኛ ዘዴ መሰጠቱ የኢንተርኔት አገልግሎት በማይኖርበት ጊዜ በተግባር የገጽ ለገጽ ትምህርት እንደሚሰጥ ጠቅሰውም፤ እንደአጠቃላይ ከመሠረተ ልማት ጋር ተያይዞ አሁንም ተጨማሪ ሥራ መስራት እንደሚጠይቅ ተናግረዋል።

# በቡታጅራ ከተማ በቀን ከ23 ሺህ ሊትር በላይ ወተት ለገበያ እየቀረበ ነው

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- በቡታጅራ ከተማ አስተዳደር በቀን ከ23 ሺህ ሊትር በላይ ወተት ለገበያ እየቀረበ መሆኑን የከተማ አስተዳደሩ የከተማ ግብርና ጽህፈት ቤት አስታወቀ፡፡

የጽህፈት ቤት ኃላፊው አቶ ሰይፉ መንጌ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በከተማ አስተዳደሩ በርካታ የከተማ ግብርና ሥራዎች እየተከናወኑ ነው፡፡ በዚህም ከተማዋ በየቀኑ ከ23 ሺህ ሊትር በላይ ወተት ለገበያ እየቀረበ ይገኛል፡፡

በተለይ የሌማት ቱርፋት ንቅናቄ ይፋ መደረጉ ለከተማዋ ትልቅ እድል መፍጠሩን አስታውሰው፤ ብዙ ዜጎች በእንስሳት ልማትና ወተት ልማት፣ በዶሮ እርባታ፣ በንብ ማነብና በአረንጓዴ ልማት ሥራዎች ላይ ተሠማርተዋል ብለዋል፡፡

በከተማ አስተዳደሩ በበጀት ዓመቱ 20 የወተት መንደሮችን መለፍጠር ታቅዶ ሲሠራ መቆቱን አንስተው፤ እስካሁን ድረስ 18 የወተት መንደሮች መደራጀታቸውንና ውጤታማነታቸውን ለማሳደግም የወተት ላሞችን የዝርያ ማሻሻል ሥራ እየተሠራ መሆኑን አስታውቀዋል።

በቀን 23 ሺህ ሊትር በላይ ወተት ተመርቶ ለከተማዋና አጎራባች አካባቢዎችም ገበያ ጭምር እየቀረበ በመሆኑ በርካቶች ተጠቃሚ እንደሆኑ አስረድተዋል።

በወተት ልማት ብቻ ከአንድ ሺህ 900 በላይ ዜጎች ቋሚና ጊዜያዊ የሥራ እድል መፍጠር መቻሉንም ጨምረው ገልጸዋል፡፡

በተያያዘ በከተማዋ 17 ዶሮ መንደሮችን መመሥረት ተችሏል ያሉት ኃላፊው፤ በሂደቱ እስከ አራት ሺህ እንቁላል ጣይ ዶሮዎችን የሚያረቡ ዜጎች መኖራቸውን ተናግረዋል።

በተጨማም በንብ ማነብ ሥራ ትልቅ ውጤት መመዝገቡን ጠቁመው፤ በዚህም ከትንሽ ነገር ተነስተው እስከ ሦስት ሚሊዮን ብር ካፒታል ማፍራት የቻሉ ወጣቶች ተፈጥረዋል ብለዋል፡፡

ከአረንጓዴ ልማት ጋር በተገናኘም አበረታች ሥራዎች እየተሠሩ መሆኑን ተናግረው፤ በከተማ አስተዳደሩ የፍራፍሬ፣ ደን የከተማ ውበት የሚውሉ ችግኞች የሚፈሉባቸው ከ12 በላይ ችግኝ ጣቢያዎች መኖራቸውን አስታውቀዋል።

መንግሥት ለልማት ሥራዎቹ የግብዓት አቅርቦት፣ መሥሪያ ቦታ ማመቻቸትና ሙያዊ ሥልጠናዎችን መስጠት ጨምሮ አስፈላጊ እገዛዎችን እያደረገ መሁኑን አስረድተዋል።

በተገኙ ውጤቶች ምክንያት ብዙዎች ወደሌማት ትሩፋት ሥራዎች ለመግባት ፍላጎት እያሳዩ መሆኑን ጠቁመው፤ ከተማ አስተዳደሩም ወደ ሥራ መግባት የሚፈልጉ ዜጎችን የማደራጀት፣ ቦታዎችን የመምረጥና ምቹ ሁኔታዎችን የመፍጠር ሥራ እየሠራ ነው ብለዋል፡፡

የሥራ ዕድል ከመፍጠር ጎን ለጎን የገበያ እድሎችን የማመቻቸት ሥራ እየተከናወነ ነው ያሉት አቶ ሰይፉ፤ በወተት ልማትና ዶሮ እርባታ ላይ ለተሠማሩ ዜጎች የመኖ አቅርቦትና የዋጋ መናር እንቅፋት መፍጠሩን አንስተዋል፡፡ ለዚህም በከተማ አስተዳደሩ ውስጥ የመኖ ማቀነባበሪያ እንዲኖር እየተሠራ መሆኑን አመላክተዋል።

# በክልሉ 400 የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች እየተከናወኑ ነው

**ክፍለዮሐንስ አንበርብር**

ጋምቤላ፡- በጋምቤላ ክልል ከ400 በላይ በተለያዩ ደረጃዎች የሚገኙ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች በሥራ ላይ መሆናቸውን የክልሉ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን አስታወቀ፡፡

የጋምቤላ ክልል ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ኮሚሽነር ዶክተር ሎው ኡቡፕ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለፁት፤ ክልሉ ውስጥ ሰፊ ኢንቨስትመንት እየተከናወነ ሲሆን በአሁኑ ወቅት በጋምቤላ ክልል ከ400 በላይ በተለያዩ ደረጃዎች የሚገኙ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች በሥራ ናቸው፡፡ በእነዚህ ፕሮጀክቶች ከአንድ ሺህ በላይ ዜጎች ቋሚ ሥራ ዕድል ተፈጥሮላቸዋል፡፡

እንደ ኮሚሽነሩ ገለፃ፤ በክልሉ ለግብርና ተስማሚ የሆነ መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ አለ፡፡ በተለይ ደጋ፣ ወይና ደጋ እና ቆላ የአየር ንብረት ያለው ክልል በመሆኑ ለአልሚዎች ጥሩ ዕድልና አማራጭ ይሰጣል፡፡

ክልሉ ሰፊ የእርሻ መሬት መኖሩን ለአብነት የጠቆሙት ኃላፊው፤ ሦስት ነጥብ 24 ሚሊዮን ሄክታር መሬት የቆዳ ስፋት ውስጥ 800 ሺህ ሄክታር በላይ የሚሆነው በእርሻ የሚለማ መሬት መሆኑን አስረድተዋል፡፡

በክልሉ በመስኖ ሊለማ የሚችለው መሬትም በጣም ሰፊ መሆኑን ጠቅሰው፤ በግብርናና ኢንቨስትመንት በተለይም በቆሎ፣ ማሽላ፣ ሩዝ፣ ማሾ፣ ወዘተ የሚመረት መሆኑ፤ በደጋማው አካባቢ የገበያ ምርቶች ቡና፣ ማር፣ ሻይ ቅጠል፣ ቅመማ ቅመም ሰፊ የኢንቨስትመንት ዕድል የፈጠሩ መሆኑን አስገንዝበዋል፡፡

በማዕድን ዘርፍም ዲማ ወረዳ እና ሌሎች አካባቢዎችን ጨምሮ ከፍተኛ አቅም ያላቸው የውጭ ሀገር አልሚዎች ወደ ሥራ መግባታቸውንና ለሀገርም ትልቅ ትርጉም ያላቸው ሥራዎች እየተከናወኑ እንደሚገኙ አስረድተዋል፡፡

በእንስሳት ሀብት፣ ዓሳ እና ሌሎች የኢንቨስትመንት አማራጮችም በክልሉ ትኩረት የተሠጣቸው መሆኑን አስረድተዋል፡፡

እንደ ዶክተር ሎው ከሆነ፤ ከለውጡ በፊት በክልሉ ከ200 በላይ ባለሀብቶች የነበሩ ሲሆን፤ ከእነዚህ ውስጥ አብዛኞቹ ብድር ወስደው ለሌላ ዓላማ የመጠቀምና ለክልሉም ብሎም ለፌዴራል መንግሥት አስቸጋሪ የሆነ ሁኔታ ውስጥ ገብተው እንደነበር አስታውሰዋል፡፡

በተለይም ሰፋፊ እርሻ ቦታ በመያዝና ከልማት ባንክ በመበደር ለተፈለገው ዓላማ ሳያውሉ በመቅረታቸው ኢንቨስትመንቶቹ ለመልካም አስተዳደር እጦት መንስዔ ሆነው ነበርም ብለዋል፡፡

በአሁኑ ወቅት የክልሉ መንግሥትም ሆነ የፌዴራል መንግሥት የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶቹን ሕጋዊ አሠራር በማስያዛቸው ጤናማ አሠራሮች መኖራቸውን ገልፀዋል፡፡

የክልሉ መንግስትም ሆነ የፌዴራል መንግሥት በተለያዩ መንገዶች ገቢ እያገኙ ሲሆን ወደ ውጭ ከሚላኩ ምርቾች ደግሞ ከፍተኛ ውጭ ምንዛሪ ማግኘት እየተቻለ መሆኑን አረጋግጠዋል፡፡

# ከመኸር እርሻ...

ከ 1ኛ ገፅ የዞረ

ሶስት ጊዜ ማለትም በበጋ መስኖ ልማት፣ በበልግና በመኸር እርሻ ምርትን የማምረት ሥራ እየተሠራ ነው ያሉት አቶ ከበደ፤ በ2016/17 በመኸር እርሻ 20 ነጥብ አራት ሚሊዮን ሄክታር መሬት አርሶ በዘር በመሸፈን 616 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ለማግኘት የማሳ ዝግጅትና ግብዓት የማቅረብ ሥራ እየተሠራ ነው ሲሉ ተናግረዋል፡፡

በ2016/17 በመኸር እርሻ 20 ነጥብ አራት ሚሊዮን ሄክታር መሬት በማረስ 616 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ለማግኘት ታቅዶ እየተሠራ ባለው ሥራ እስከ ሰኔ 10/2016 ዓ.ም ድረስ አስራ ሶስት ነጥብ 6 ሚሊዮን ሄክታር መሬት የመጀመሪያ እርሻ የማረስ ሥራ መከናወኑን አብራርተዋል፡፡

የመጀመሪያ እርሻ ከታረሰው 13 ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ሄክታር መሬት ውስጥ አራት ሚሊዮኑ በትራክተር የታረሰ ሲሆን ዘጠኝ ነጥብ አምስት ሚሊዮን ሄክታር መሬት የሚሆነውን በባህላዊ መንገድ የማረስ ሥራ ተከናውኗል ሲሉ አብራርተዋል፡፡

በተጨማሪም አራት ነጥብ አራት ሚሊዮን ሄክታር መሬት ቅድሚያ በሚዘሩ አዝርዕቶች ማለትም በበቆሎ፣ በማሽላና በተለያዩ ሰብሎች የመሸፈን ሥራ ተሠርቷል ሲሉ ገልጸዋል፡፡

አርሶ አደሩ ምርትና ምርታማነቱን ለማሳደግ እርሻ ማሳውን የማዘጋጀት፣ የማለስለስ ስራ እየሠራ ነው ብለው፤ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱም ለግብርናው ምርት ማደግ የሚረዱ ግብዓቶችን የማቅረብ እና ግንዛቤ የማስጨበጥ ሥራ በስፋት እየሠራ ነው ብለዋል፡፡

በ2016/17 የምርት ዘመን ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ 14 ሚሊዮን ኩንታል የአፈር ማዳበሪያ ወደ ሀገር ውስጥ ገብቶ ለአርሶ አደሩ ተደራሽ የማድረግ ሥራ እየተሠራ መሆኑንም አብራርተዋል፡፡

ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ አርሶ አደሩ ከቀረበለት አስራ አራት ሚሊዮን ኩንታል የአፈር ማዳበሪያ በተጨማሪ ኮምፖስት በማዘጋጀት የእርሻ ማሳውን ለዘር የማዘጋጀት ሥራ እየሠራ ነው ሲሉ አብራርተዋል፡፡

እየዘነበ ያለው ዝናብ ለመኸር እርሻ ዝግጅት አመች በመሆኑ አርሶ አደሩ ምርትና ምርታማነቱን ለማሳደግ በንቃት እየሠራ ነው ሲሉ ገልጸዋል፡፡

እስከ ሀምሌ ወር መጨረሻ ድረስ አብዛኛውን የሀገሪቱን የእርሻ መሬት በሰብል ዘር በመሸፈን በ2016/17 የመኸር እርሻ ለማግኘት የታቀደውን 616 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ለማግኘት ሰፊ ዝግጅት እየተደረገ ነው ሲሉ ጠቁመዋል፡፡

# የኢኮኖሚ ልዩ ዞን ሥርዓት ለኢትዮጵያ...

ከ 1ኛ ገፅ የዞረ

በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የኢኮኖሚ ልዩ ዞን አዋጅ መጽደቁ ይታወሳል።

የተለያዩ የዓለም ሀገራት የኢኮኖሚ ልዩ ዞን ሥርዓትን የኢኮኖሚ እድገታቸውን ለማፋጠን፣ ኢንቨስትመንትን ለመሳብ እንዲሁም ቀልጣፋና አመቺ የንግድ ሁኔታን ለመፍጠር የሚጠቀሙት አንዱና ዋነኛ መሣሪያቸው ነው።

ከዚህ አንፃርም በኢትዮጵያ የጸደቀው የኢኮኖሚ ልዩ ዞን አዋጅ የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ለማሳደግ፣ ቀልጣፋና አመቺ የኢንቨስትመንትና የንግድ ሁኔታ ለመፍጠር ትልቅ ሚና እንደሚጫወትም ሲነገር ቆይቷል።

ለመሆኑ የኢኮኖሚ ልዩ ዞን ሥርዓት ለአንድ ሀገር ያለው ፋይዳ ምንድነው፣ አዋጁን ተግባራዊ ለማድረግ ከማን ምን ይጠበቃል፣ የሚሉ ጉዳዮች ላይ ኢፕድ ያነጋገራቸው የምጣኔ ሀብት ምሁራን ሃሳባቸውን ሰጥተዋል።

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የምጣኔ ሀብት መምህር የሆኑት ዶክተር ብርሃኑ ደኑ፤ የኢኮኖሚ ልዩ ዞን በሀገራችን አዲስ እንዳልሆነና በተለያዩ አካባቢዎች ሲተገበር መቆየቱን ያነሳሉ።

የኢኮኖሚ ልዩ ዞን በአንድ ሀገር ሲታሰብ ፈጣን የሆነ ኢኮኖሚያዊ ለውጥ ለማምጣት ታልሞ ራሱን የቻለ ሕግ ወጥቶለት የሚተገበር ነው የሚሉት ዶክተር ብርሃኑ የኢኮኖሚ ልዩ ዞን ዋናው ዓላማ የሚሆነውም በጂኦግራፊ በተገደበ አካባቢ ውስጥ ፈጣን የሆነ ኢኮኖሚያዊ ልማት ማስገኘት ነው ሲሉ ይገልጻሉ።

የኢኮኖሚ ልዩ ዞን ሥርዓት ከሌሎች ለየት የሚያደርገው መንግሥት እነዚህ ልዩ ዞኖች ላይ የሚጥለው ታክስ አነስተኛ መሆኑ እንደሆነ የሚናገሩት



ዶክተር ብርሃኑ፤ ይህም አስቻይ የሆነ የመንግሥት ልዩ ድጋፍ የሚጸባረቅበት ነው ይላሉ።

መንግሥት ለነዚህ የኢኮኖሚ ልዩ ዞኖች የሚያደርገው ድጋፍ ባለሀብቶች መዋዕለ ንዋያቸውን በዚያ አካባቢ ያለስስት እንዲያፈሱ ከማድረግ ባሻገር የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንትን የሚጨምር መሆኑንም ያስረዳሉ።

ከሁለት ዓመት በፊት በተጠና ጥናት በዓለም ላይ ከሰባት ሺህ በላይ የኢኮኖሚ ልዩ ዞን እንደሚገኙ የሚናገሩት ዶክተር ብርሃኑ፤ ይህም ለአንድ ሀገር ኢኮኖሚ ምን ያህል ጠቃሚ መሆኑን ማሳያ ነው ሲሉ ያስረዳሉ።

የኢኮኖሚ ልዩ ዞን በሌሎች የዓለም ሀገራት ለረዥም ዓመታት ሲተገበር መቆየቱን የሚያነሱት መምህሩ በዚህ ሥርዓት ከፍተኛ የኢኮኖሚ እድገት ካስመዘገቡ ሀገራት መካከል ቻይና በዋነኝነት የምትጠቀስ መሆኗን ይናገራሉ።

በሀገራችንም እነዚህ የኢኮኖሚ ልዩ ዞኖች ሲታሰቡ ከፍተኛ የሥራ አድል እንደሚፈጥሩ እንዲሆኑ፣ ከፍተኛ የውጭ ኢንቨስትመንት ለመሳብ የሚያግዙ እና ወጪ ንግዱን በማሻሻል ሀገሪቱ ያለባትን ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ እጥረት ለመቅረፍም ነው ይላሉ። ዶክተር ብርሃኑ እንደሚገልጹት፤ መንግሥት የሥርዓቱን ጠቀሜታ ተረድቶ አዋጅ አጽድቆ ወደ ሥራ ሲገባ አዋጁ ተፈጻሚ እንዲሆን መሥራት የሚኖርበት የቤት ሥራዎች ይኖራሉ ። በልዩ ዞኖች መዋለ ንዋያቸውን ለሚያፈሱ ባለሀብቶች አስቻይ የሆኑ ሕጎችን ማውጣትና በተለይም የታክስ ቅነሳ ላይ መንግሥት የሚያደርገውን ልዩ ድጋፍ ማጠናከር ይኖርበታል። አለበለዚያ የተጠበቀውን ያህል ውጤታማ መሆናቸው ጥያቄ ውስጥ እንደሚገባ ስጋታቸውን አጋርተዋል።

የኢኮኖሚ ልዩ ዞን ሥርዓትን በተለይም እያደጉ ያሉ ሀገራት ቀጣይነት ባለው መልኩ ኢኮኖሚያቸውን ለማሳደግ ይጠቀሙበታል የሚሉት ደግሞ ሌላኛው የምጣኔ ሀብት ምሁሩ ዶክተር ይንገስ አለሙ ናቸው።

ዶክተር ይንገሥ፤ በአንድ ሀገር የኢኮኖሚ ልዩ ዞን ሥርዓት ተግባራዊ መሆኑ አምራች ኢንዱስትሪዎች የሚፈልጉትን የኢንዱስትሪ ግብዓቶችን በቅርብ ርቀት ለማግኘት ባለፈ ለባለሀብቶች ምቹ ሁኔታ የሚፈጥርና የውጭ ቀጥተኛ ንግድን የሚያጎለብት ነው ሲሉ ያብራራሉ።

ይህ የኢኮኖሚ ልዩ ዞን ሥርዓት ቻይና እና ደቡብ አሜሪካ ኢኮኖሚያቸውን ለማሳደግ ከተጠቀሙበት ስትራቴጂ ውስጥ በዋናነት የሚጠቀስ መሆኑን የሚገልጹት ዶክተር ይንገሥ በዚህ ሥርዓት ሀገራቱ ለባለሀብቶች የተለያዩ ልዩ ድጋፎችን በማድረግ ባለሀብቶች ለመሳብ ተጠቅመውበታል ሲሉ ይገልጻሉ።

የኢኮኖሚ ልዩ ዞን ሥርዓት ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት ሚያመጣ አንድ መሣሪያ መሆኑን የሚናገሩት ዶክተር ይንገሥ ሆኖም የሚኖሩ ተግዳሮቶች እንዳሉም ያነሳሉ።

መንግሥት ይህን የኢኮኖሚ ልዩ ዞን ሥርዓት ሀገሪቱ ላይ ተግባራዊ ሲያደርግ የሚኖሩ ተግዳሮቶችን ለመቀልበስ በተለይም ታክስ፣ ታሪፍ እንዲሁም ማበረታቻዎች ላይ ትኩረት አድርጎ ሊሠራ ይገባል ሲሉ አስተያየታቸውን ይሰጣሉ።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ከተረጂነት እና የተረጂነት አስተሳሰብ ራሳችንን ነጻ ማውጣት ይጠበቅብናል

ተረጂነት በአንድ ሀገር /ሕዝብ ማኅበራዊ ስነ ልቦናም ሆነ ብሔራዊ ክብር ላይ ሊያሳድር የሚችለው አሉታዊ ተጽእኖ ከፍተኛ ነው። በተለይም የተለያዩ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ ፍላጎቶችን በሌሎች ላይ ለመጫን የሚያስችሉ ሴራዎች በስፋት በሚስተናገድበት አሁናዊ ዓለም አቀፍ እውነታ ውስጥ ተረጂነት ሊያስከትል የሚችለው ጥፋት አጠቃላይ የሀገራትን ቀጣይ ዕጣ ፈንታን አደጋ ላይ የሚጥል እንደሚሆን ይታመናል።

የአንድን ሀገር ሉዓላዊነት ምሉዕ ከሚያደርጉ ጉዳዮች አንዱ፤ ሀገራቱ የራሳችውን ዕድል በራሳቸው የመወሰን ሁለንተናዊ አቅም የመገንባታቸው እውነታ ነው። የኔ የሚሉትን ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ እሴቶች የማጽናት እና የማስቀጠል ጉልበት ሲፈጥሩ፤ በተጨባጭ ተግባራዊ በማድረግ ማኅበረሰባዊ ማንነታቸውን አጠንክረው መቀጠል ሲችሉ ነው።

ይህንን ማድረግ ያልቻለ ሀገር /ማኅበረሰብ የጊዜ ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር በተለያዩ የአስተሳሰብ መዛነፎች እና እነሱን በሚደግፉ ዓለም አቀፍ ሴራዎች ማንነታቸው እየተሸረሸረ ራሳቸውን መሆን የማይችሉበት እውነታ መፈጠሩ የማይቀር ነው። ይህ ደግሞ ራስን ካለመሆን ለሚፈጠር የማንነት ዝቅጠት መዳረጉ፤ ብሔራዊ ክብርንም ማጠልሸቱ ብዙም ለጥያቄ የሚቀርብ አይደለም።

ለዚህ ዓይነቱ ፈተና ከሚዳርጉ ችግሮች አንዱ እና ዋነኛው፤ በአንድም ይሁን በሌላ ሊፈጠር የሚችል የተረጂነት መንፈስ ነው ።ተረጂነት በራሱ ችግር አይደለም፤ በተለያዩ አጋጣሚዎች ሊፈጠር የሚችል ክስተት ነው። ከዚህ ባለፈ ተረጂነት የህይወት ጉዞ አንድ አካል አድርጎ መውሰድ ፤ ማህበረሰባዊ ማንነትን የሚያኮስስ፤ ብሄራዊ ክብርን የሚያጎድፍ ጥልቅ መርገም ነው ።

በተለይም ባለንበት ዘመን እርዳታን ከሰብአዊነት ባለፈ የፖለቲካ መሳሪያ አድርጎ የመጠቀም ዓለም አቀፍ ልምምድ በስፋት በሚስተዋልበት ፣ እርዳታዎች በብዙ አድርግ አታድርግ አስገዳጅ ትእዛዛት ተቃኝተው እየመጡ ባለበት ዓለም አቀፋዊ እውነታ፤ የተረጂነት መንፈስ ሊፈጥር የሚችለው ብሄራዊ አደጋ ከግምት በላይ ነው።

ችግሩ በሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ስም እርዳታ ተቀባይ ሀገራት ለዘመናት ያካበቷቸውን መንፈሳዊ እና ባህላዊ እሴቶች እየተፈታተኑ ያለበት ሁኔታ የአደባባይ ምስጢር ከሆነ ውሎ አድሯል። ሀገራቱ ጤናማ አምራች ትውልድ ለመፍጠር ለሚያደርጉት ጥረትም ፈተና እንደሆነ ነው ።

ሀገራት አስከፊ በሆኑ ተፈጥሯዊ እና ሰው ሰራሽ ችግሮች ፈተና ውስጥ በወደቁባቸው ጊዜያት ፣ የዜጎቻቸውን ህይወት ለመታደግ ዓለም አቀፍ እርዳታዎችን በሚጠይቁባቸው ወቅቶች ሳይቀር፤ ለሚጠይቋቸው የሰብአዊ ድጋፎች ፣ በሕዝባቸው መከራና ስቃይ እንዲደራደሩ የሚገደዱባቸው ሁኔታዎች እየተበራከቱ ነው።

አሁን አሁን እነዚህን ክፉ ቀናትን እንደ መልካም አጋጣሚ በመጠቀም በመልካም ቀናት ማስፈጸም ያልቻሉትን ፍላጎታቸውን በእርዳታ እና ድጋፍ ስም በሀገራት ላይ ለመጫን የሚንቀሳቀሱ፤ ይህንንም ስትራቴጂክ የማስፈጸም አቅም አድርገው የሚወስዱ ሀገራት ፣ ተቋማት እና ቡድኖች ጥቂት አይደሉም።

ከዚህም ባለፈ ሀገራት ራሳቸውን ችለው በራሳችው ዕጣ ፈንታ ላይ ወሳኝ ኃይል እንዳይሆኑ፤ ተረጂነትን ተቀብለው በጠባቂነት እንዲኳዙ የሚደረጉ ዓለም አቀፍ ሴራዎች በቀላሉ የሚታዩ አይደሉም፤ ነገሮች እንደማይቻሉ አድርጎ ማሰብ የሚያስችል ማኅበረሰባዊ የስነ ልቦና ጫና ከመፍጠር ጀምሮ በግጭቶች ሀገራትን ዕረፍት መሳጣት የዚሁ ሴራ መገለጫዎች ናቸው።

በርግጥ በዓለማችን የሚጠቀሱ አብዛኞቹ ተረጂ ሀገራት ፣ ካላቸው ሀገራዊ አቅም አኳያ ከራሳቸው አልፈው ለሌሎች መትረፍ የሚያስችል ሁለንተናዊ ቁመና ያላቸው ናቸው። በተለያዩ የታሪክ አጋጣሚዎችም ይህን አቅማቸውን ተጠቅመው ለብዙዎች መትረፍ የቻሉም ናቸው። በሀገራቱ ሕዝቦች ስነ ልቦና ላይ ከተጫነ የአይቻልም መንፈስና በሴራ በተፈጠረ የሰላም እና የመረጋጋት እጦት ለተረጂነት ተዳርገዋል።

በታሪክ ሂደት ውስጥ ይህ የተረጂነት መንፈስ የተረጂነት ስነልቦና በመፍጠር ሀገራቱ ተረጂነትን ተቀብለው እንዲኖሩ ፣ ተረጂነት ለሚፈጥረው የማንነትም ሆነ የብሔራዊ ክብር ዝቅታ ራሳቸውን እንዲያለምዱ አድርጓቸዋል። ማንነታቸውን እና ብሔራዊ ክብራቸውን ብቻ ሳይሆን ሰብአዊ እሴቶቻቸውንም ጭምር ከእጃቸው በሚያሳጣ ታሪካዊ አጋጣሚ ውስጥ እንዲገኙ አድርጓቸዋል።

ይህ ዓለም አቀፍ እውነታ እኛንም እንደ ሀገር እየተፈታተነ ስለመሆኑ፣ ከእያንዳንዷ ሰብአዊ ድጋፍ በስተጀርባ በሰብአዊ መብት እና በዴሞክራሲ ስም የሚመጡ ይህን አድርግ አታድርግ ትእዛዛት መመልከቱ በራሱ በቂ ነው። ትእዛዛቱን ባለመፈጸማችን እያጋጠሙን ያሉ ፈተናዎች የቱን ያህል ዋጋ እያስከፈሉን መሆናቸውም የአደባባይ ምስጢር ነው።

እንደ ሀገር ከዚህ ችግር ለዘለቄታው ለመውጣት፤ የራሳችንን ዕድል በራሳችን በመወሰን ራሳችንን ሆነን ቀጣይ የታሪክ ምዕራፋችንን ብሩህ አድርገን፣ ብሔራዊ ማንነታችንን አጽንተን፣ ብዙ ዋጋ የተከፈለበትን ሀገራዊ ክብራችንንና ነጻነታችንን አስጠብቀን ለመጓዝ ከተረጂነት እና ከተረጂነት አስተሳሰብ ራሳችንን ነጻ ማውጣት ይጠበቅብናል።

ለዚህ ደግሞ በለውጡ ማግስት ከድህነት እና ድህነት ከሚፈጥረው ጠባቂነት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ለመውጣት የጀመርነውን ሀገራዊ መነቃቃት ማስቀጠል ፣ መነቃቃቱ የፈጠረውን ተጨባጭ ተስፋ በማጤንም ለበለጠ ሥራ ራሳችንን ማዘጋጀት ብሎም ለዚህ የሚሆን ቁርጠኝነት መፍጠር ይኖርብናል!


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ለከተማዋ ፅዳት የነዋሪነት ግዴታችንን እንወጣ

**ይቤ ከደጃች ውቤ**

መዲናችን ሀገር የሚያውቀው ፀሐይ የሞቀው የመጸዳጃ ቤት ችግር አለባት፡፡ ከዚህ የተነሳም በየቦታው ሰው አየን አላየን እያለ የሚሸና ፣ ሸሸግ ያለ ቦታ እየፈለገ ወገቡን የሚሞክር ጥቂት አይደለም። አሁን አሁን ደግሞ በሃይላንድ የውሃ መያዣ ላስቲክ ሽንቱን እየሸና እየከደነ አስፋልት ላይ የሚጥልም እየተበራከተ ነው፡፡

ችግሩ አሁን ላይ ለከተማዋ ጥልቅ ፈተና እየሆነ ነው። ችግሩን ለዘለቄታው ለመፍታት በቅርቡ ‹‹ፅዱ ጎዳና ኑሮ በጤና›› የተባለ የዲጂታል ንቅናቄ በጠቅላይ ሚኒስትሩ ዐቢይ አሕመድ አማካይነት ይፋ ሆኗል፡፡ ቴሌቶኑ ችግሩን በመቅረፍ ሂደት ውስጥ የጎላ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው ይታመናል።

> **እያንዳንዱ የከተማዋ ነዋሪ ከተማዋ ንጹህ ከመሆኗ ጋር በተያያዘ ሊያገኝ የሚችለውን ሁለንተናዊ ተጠቃሚነት በአግባቡ የሚያጤንበት ሥርዓት ሲዘረጋ ይገባል**

ንቅናቄው በቀዳሚነት ሰዎች በመጸዳጃ ቤት መጠቀም የሚችሉበት እድል ያመቻቻል፤ በመጸዳጃ ቤቱ ተቀጥረው ለሚሠሩ ዜጎች የሥራ ዕድል ያስገኛል፣ የመዲናዋ ጎዳናዎች ጽዱ፣ ውብና መስህብ የተላበሱ እንዲሆኑ፤ ነዋሪውም ሆኑ ጎብኚዎች በከተማዋ ጉዳናዎች በተሻለ መንገድ እንዲንቀሳቀሱ ያስችላቸዋል።

እጃችንን አፋችን ላይ ጭነን የአዲስ አበባ ጎዳና እየተዘዋወርን መዲና እንደስምዋ ሆነች ማለት የሚያስችለንን እድል ይፈጥርልናል፤ ሸተተኝ ብለን እጃችንን አፍንጫችን ላይ ከመጫንም እንታቀባለን፡፡ በቆሻሻ ምክንያት ሊፈጠሩ ከሚችሉ የጤና ችግሮች እራሳችንን መታደግ እንችላለን፡፡

በአዲስ አበባ ከንጉሱ ዘመነ መንግሥት ጀምሮ፤ በፒያሳ አራዳ ሕንፃ አካባቢ፣ በመርካቶ ሳጥን ተራ ማለትም ከአመዴ ገበያ ሕንፃ ጀርባ፣ በሸራ ተራ፣ በምናለሽ ተራ፣ ወደ መሳለሚያ መንገድ አካባቢ፣ በኳስ ሜዳ፣ በአራዳ የሕዝብ መጸዳጃ ቤቶች ነበሩ። መጸዳጃ ቤቶቹ በማዘጋጃ ቤት የተገነቡና ተቀጣሪ ሠራተኞች የነበራቸው፤ ለሕዝብ በነፃ አገልግሎት የሚሰጡ ናቸው፡፡

አብዛኞቹ አሁን ላይ ተዘግተው ከአገልግሎት ውጪ ሆነዋል፡፡ ‹‹ፅዱ ጎዳና ኑሮ በጤና›› ንቅናቄ ሲተገበር የጠቀስኳቸውን የመሳሰሉ የተዘጉ የሕዝብ መጸዳጃ ቤቶች በድጋሚ ታድሰው ለአገልግሎት ብቁ ቢሆኑ ሸጋ ነው፡፡

በተለይም በቅርብ ጊዜ የተገነቡ ለመንገደኞች ሦስት ብር ከፍለው አገልግሎት ሲሰጡ የነበሩ አሁንም ያሉ መጸዳጃ ቤቶች አሉ፡፡ የአገልግሎት አሰጣጣቸው ላይ ያለው ችግር እንዳለ ሆኖ ፈረንጆቹ ‹‹አንድ ነገር ከኢምንት ነገር ይሻላል›› እንደሚሉት መኖራቸው በራሱ የሚበረታታ ነው፡፡

መጸዳጃ ቤቶቹ የሚጠይቁት የተጋነነ ክፍያ በራሱ የነዋሪውን የመክፈል አቅም ሆነ የአገልግሎቱን ጥራት ያገናዘበ ነው ወይ የሚለው በራሱ መልስ የሚፈልግ ቢሆንም የመጸዳጃ ቤት አጠቃቀማችን በራሱም ሌላ ምላሽ የሚሻ ነው፡፡ ችግሩ እንኳን በነዚህ መጸዳጃ ቤቶች በመንግሥት መሥሪያ ቤቶችም የሚስተዋል ነው፡፡ በጤና ጣቢያዎችና በሆስፒታሎች እና ጤና ጣቢያዎች ያለውም ከዚህ በብዙ የተለየ አይደለም። ታካሚ ሊጠይቁ ሄደው ታማሚ ሆነው የሚመለሱ አይጠፉም፡፡

ችግሩ በሕዝብ ትራንስፖርት መናኸሪያዎችም በስፋት የሚስተዋል ነው። መናኸሪያዎቹ ብዙ የኅብረተሰብ ክፍሎች ዘወትር የሚያስተናግዱ መሆናቸው ይታወቃል፡፡ ግን አብዛኞቹ ለተሳፋሪዎች መጸዳጃ አልባ ናቸው፡፡

መቼም ስለመጸዳጃ ቤቶች ስንናገር በከተሞቻችን ያሉ ሻይ ቡና ቤቶች፣ ምግብ ቤቶች ፣ ኬክ ቤቶች ፣ መጠጥ ቤቶችም ሆነ ሆቴሎችም ጭምር የመጸዳጃ ቤቶቻቸው ለደንበኞቻቸው በአግባቡ አገልግሎት ሊሰጡ የሚችሉበት መንገድ መታየት አለበት። አምስት ስድስት ፎቅ ሆቴል ይዘው፤ መጸዳጃ ቤቶቻቸው እዚህ ግባ የሚባሉ አይደሉም፡፡

ከዚሁ ጋር ተያይዞ በአዲስ አበባ በየወረዳው ያሉ የሕዝብ መዝናኛ ከበቦችም ትኩረት ሊደረግባቸው ያስፈልጋል፡፡ አብዛኞቹ የሕዝብ መዝናኛ ከበቦች መናኛ አገልግሎት የሚሰጡ ናቸው፡፡ ብዙ ሰው ቢራውን ድራፍቱን እየጠጣ ከአንድ የዘለለ መጸዳጃ ቤት የላቸውም፡፡ በዚያ ላይ በሁሉም መጸዳጃ ቤቶች የሚታየው ዝርክርክ አሠራር በመናኛ መዝናኛ ከበቦቹ ተባብሶ በስፋት ይታያል፡፡ ከፊሎቹ የሴቶች መጸዳጃ ቤትም የሌላቸው ናቸው፡፡

ችግሩ በመንግሥት ብቻ ሊፈታ የሚችል አይደለም ፤ከሁሉም በላይ አጠቃላይ በሆነው የከተማ ጽዳት ላይ የጋራ ግንዛቤ መፍጠር ያስፈልጋል። እያንዳንዱ የከተማዋ ነዋሪ ከተማዋ ንጹህ ከመሆኗ ጋር በተያያዘ ሊያገኝ የሚችለውን ሁለንተናዊ ተጠቃሚነት በአግባቡ የሚያጤንበት ሥርዓት ሊዘረጋ ይገባል። ይህን ማድረግ ከተቻለ ችግሩ ከከተማዋ ነዋሪ አቅም በላይ ሊሆን የሚችል አይደለም።

እስካሁን ባለው ሁኔታ ‹‹ ፅዱ ጎዳና ኑሮ በጤና›› ንቅናቄው ብዙዎች እየተሳተፉበት ነው። በንቅናቄው ከፍተኛ ተሳትፎ ካሳዩ የዳያስፖራ አደረጃጀቶች መካከል በአቡዳቢና በዱባይ የሚገኙ የዳያስፖራዎች እያንዳንዳቸው በየኮሚኒቲያቸው ስም አንድ አንድ መጸዳጃ ቤቶችን የሚያስገነባ ከ1.5 ሚሊዮን ብር ለመለገስ ተስማምተዋል።

በአሜሪካ የሚኖሩ ዳያስፖራዎች በበኩላቸው 12 መጸዳጃ ቤቶችን ለማስገንባት ቃል በመግባት፣ ከአንድ ሚሊዮን ብር በላይ ድጋፍ አድርገዋል። እኛም ለዚህ በጎ ዓላማ በመንቀሳቀስ ለከተማዋ ንጽህና የነዋሪነት ግዴታችንን ልንወጣ ይገባል፡፡ለዚህ ደግሞ ወቅቱ አሁን ነው።

## ነፃ ሃሳብ

# ጦር አውርድ - ፈውስ አልባ ልክፍት

**አሸብር ኃይሉ**

የሰው ልጅ አሁን ከደረሰበት የእድገት ደረጃ ለመድረስ በበርካታ ሰው ሰራሽ እና ተፈጥሯዊ ኩነቶች ተፈትኗል፡፡ ከሰው ሰራሽ ፈተናዎች መካከል ጦርነት በግንባር ቀደምትነት የሚጠቀስ ነው፡፡ ጦርነት ከሰው ልጅ ማህበረሰባዊ እድገት ጋር የተቆራኘ እና አብሮ የኖረ ስለመሆኑ የተለያዩ ተቋማቶች ያመላክታሉ፡፡

ጦርነት አጥፊ እና አሰቃቂ ውድመት የሚያስከትል ቢሆንም በአንጻሩ በተለያዩ ምክንያቶች ወደ ጦርነት የገቡ ህዝቦች / ሀገራት ከጦርነቶች ብዙ ተምረው ዛሬ ላይ በብዙ መንገድ የተሻለ ሕይወት ለመምራት የቻሉበትን ሁኔታዎች መፈጠራቸውንም የታሪክ መዛግብት ይናገራሉ፡፡

አውሮፓዊያን በ18 እና በ19ኛው ክፍለ ዘመን ካደረጓቸው ደም አፋሳሽ አብዮት ወለድ ጦርነቶች(የእርስ በርስ ጦርነት) በኋላ ኑሯቸውን ለማሸነፍ አዳዲስ አሰራሮችን እና መዋቅሮችን መፍጠር ችለዋል፡፡ በዚህም ኢንዱስትሪ አብዮትን በማምጣት ኑሯቸውንም አዘምነዋል፡፡ አሁን ላይ በአውሮፓ የሚገኙ ሀገራት ብሔርን ወይም ደግሞ ሌላ መስፈርትን መሰረት አድርገው የእርስ በርስ ጦርነትን አያደርጉም፡፡ ለማድረግም ፈጽሞ አያስቡትም።

አሜሪካዊያንም ካደረጉት አስከፊ የእርስ በርስ ጦርነት በኋላ ከስህተታቸው ተምረው አዳዲስ አሰራሮችን ቀመሩ፡፡ ጦርነትን አብዝተው ተጠየፉ፡፡ በአንደኛው የአለም ጦርነት ሁኔታዎች አስገድደው የጦርነቱ ተጋባዥ ቢያደርጓቸውም እነሱ ግን ግብዣውን ሳይቀበሉ ቀሩ፡፡ ሌሎች ዓለማት በጦርነቱ ኢኮኖሚያቸው አይሆኑ ሆኖ ሲደቅ አሜሪካ ግን የዓለማችን ባለግዙፍ ኢኮኖሚ ሆና ብቅ አለች፡፡

እኛ ኢትዮጵያዊያን ግን ከጦርነቶች መማር የሚባል ነገር ፈጽሞ አንፈልግም፡፡ የእርስ በርስ ጦርነቶችን በማቆም ችግሮቻችንን በሃሳብ ለመፍታት ፈጽሞ ዝግጁ አይደለንም፡፡ ስለእውነት ከእርስ በርስ ጦርነት ጋር የተገናኘ ፈውስ አልባ ደዌ የተጣባን ይመስላል፡፡ እንደሌሎች ሀገራት ከጦርነት ጥፋት መማር ራሳችንን ከጦርነት ማራቅ ተስኖን ዘመናት እየቆጠርን ነው።

ከግራ ከቀኝ፤ ከላይ ከታችም ካሉ ኢትዮጵያዊያን የበለጠ የጦርነትን አስከፊነት የሚያውቅ ያለ አይመስለኝም፡፡ ነገር ግን ዛሬም ችግሮችን በንግግር እና በምክክር ከመፍታት ይልቅ ሁሉን ነገር በጦርነት ለመፍታት ስንጥር እንታያለን፡፡ «አዞ በሞላበት ኩሬ ካልዋኘን» ብለን ለያዥ ለገናዥ እናስቸግራለን፡፡

«ጦር አውርድ!» እንላለን፡፡ «መንገድ ሳለ በዱር በቅሎ ሳለ በግር» እንዲሉ ሀገራችን ሁሉ ነገር ሞልቷት፤ ችግሮችን በንግግር መፍታት ሲቻል ሁልጊዜ የእርስ በርስ ጦርነት ውስጥ ለመግባት እንሽቀዳደማለን፡፡ ሰለምን በርካታ አማራጮች እያሉ ጦርነትን የሁሉም አማራጭ እናደርገዋለን? እንዴት «መንገድ ሳለ በዱር በቅሎ ሳለ በግር» እንመርጣለን? እስከመቼ ጦር አውርድ!? እስከመቼ ኢትዮጵያስ በልጆቿ ማስተዋል ማነስ ትጎሳቆል!?

«ሞኝን ሁለት ጊዜ እባብ ነደፈው ፤ አንድም የእባብን ተናዳፊነት ሳያውቀው ነካክቶት ሁለትም ይህ ነው የነደፈኝ ብሎ ለሌሎች ሰዎች በእጁ ነክቶ ሲያሳይ» አሉ፡፡ እኔ የምለው እስከመቼ ነው አንድ ጊዜ የነደፈንን እባብ ተናዳፊነት ለሰዎች ለማሳየት በእጃችን እየነካካን የምናሳየው?

**ሁሌም ሰላም እንዲኖር ሁላችንም አበክረን መስራት ይኖርብናል፡፡ በየትኛውም ሁኔታ ሰላም ለሁሉም ነገር ቅደመ ሁኔታ እንጂ ለሰላም ምንም ቅድመ ሁኔታ ማበጀት የለብንም**

አሁን በሀገራችን በብዛት እየተስተዋለ ያለው ጦርነት ደግሞ ለውሽማ ሞት ፊት አይነጭለት አይነት ነው፡፡ የአንዱ ብሔር መሞት እና መጎሳቆል ለሌላው እንደምን ነው። ይባስኑ ሌሎች ብሔሮች ሌላ ጦር አውርድ የሚሉ ይመስላል፡፡ ይህ ትክክል አይደለም፡፡

ጦር አውርድ የሚለውን ሃሳብ ሳነሳ አጼ ልብነ ድንግልን ያስታውሰኛል፡፡ አጼ ልብነ ድንግል በዘመነ መንግሥታቸው ጠንካራውን እና ታዋቂውን የአዳል ሱልጣን ማህፉዝ (ማኅፉድን) ገደሉ። የመንግሥታቸውን ጠንካራ ተቀናቃኝ የገደሉት ንጉሱ አስተማማኝ በሚባል ደረጃ መንበረ ስልጣናቸውን አጸኑ። በኢትዮጵያ አጼ ልብነ ድንግልን በኃይል የሚገዳደር ጠፋ። በኢትዮጵያም ሰላም፣ ጥጋብ እና ደስታ ሆነ፡፡

በዚህ ጊዜ የንጉሱ መኖሪያ ቦካን የሚባል ሀገር ነበር፡፡ ቀንን ቀን ሲወልደው አጼ ልብነ ድንግል «ጭር ሲል አልወድም፤ ጦር አውርድ!» አሉ፡፡ በቦካን እያሉ «ጦር አውርድ» እያሉ ከመኳንንቶቻቸው ጋር የፈርስ ጉግስ እያደረጉ የራሳቸውን መኖሪያ ግንብ በጦር ይወጉ ነበር። ከእለታት በአንድ ቀንም ችግር የበዛበት የንጉሱ መኖሪያ ግንብ ተደርምሶ በግንቡ ስር የነበሩ ነዳያኖችን ተጭኖ ገደለ፡፡ ግንቡን በጦር ሲወጉ የነበሩት ንጉሱ እና መኳንንቶቻው «ጦር አውርድ» እያሉ መሬትንም በዱላ ይደበድቡ ነበር፡፡

ይህም አልበቃቸው ጦርነት ይመጣላቸው ዘንድ ለጣና ቂርቆስ እና ለደብረ ሊባኖስ ገዳማት አንድ አንድ ጫን (15 ማዳበሪያ) እጣን ላኩ። ለገዳማቱ አባቶችም «ጦርነት እንዲመጣ ጸሎት አድርጉልኝ» አሉ። አባቶችም ንጉሱ የሚሰሩት ስራ ትክክል አለመሆኑን ነገሯቸው። ነገር ግን ሰሚ አልተገኘም፡፡

በመጨረሻም የለመኑትን የማይነሳ ፈጣሪ አህመድ ግራኝን አስነሳባቸው፡፡ አህመድ ግራኝ በተነሳ ጊዜ ለጦርነት ከፍተኛ ጉጉት የነበራቸው ንጉሱ ሐረር ድረስ ሂደው ገጠሙ፡፡ ነገር ግን ተሸነፉ፡፡ ወደኋላም ሸሹ። ድል ፈጽሞ ራቃቸው ፡፡ አህመድ ግራኝ የማይቆረጠም የጠጠር ቆሎ ሆነባቸው፡፡ በሚሸሹበት ሁሉ እየተከታተለ አጠቃቸው፡፡

ከአጼ ገላውዴዎስ ቀጥሎ አጼ ሚናስ ተብሎ የነገሰውን ልጃቸውንም ማርኮ ቱርክ ሀገር ለባርነት ሸጠው፡፡ «ጦር አውርድ» ብለው ፈጠሪን ሲለምኑ እና ሲያስለምኑ የነበሩት ንጉስ ልጆቻቸውን እንኳን ከባርነት መታደግ ሳይችሉቀሩ፡፡

ይህ ክፉ ልክፍት ተጣብቶ አለቅ ያላቸው ኢትዮጵያዊያን ካለፈው ጊዜ ሳይማሩ ቀርተው ዘመነ መሳፍንትን አመጡ፡፡ ከዘመነ መሳፍንት መማር የተሳናቸው ኢትዮጵያዊያን ከአጼ ቴዎድሮስ እስከ ዛሬ እርስ በርስ መዋጋትን ስራዬ ብለው የያዙት ይመስላሉ። አዞ በበዛበት ኩሬ መዋኘትን ምርጫቸው አድርገዋል፡፡

«ሀ ባሉ ተዝካር ይበሉ» እንዲሉ ሁልጊዜም በእኛ ሀገር ጦርነት የሚነሳው ትንሽ ፊደል በጠነቆሉ ፖለቲከኛ ነን ባይ ፍርፋሪ ለቃሚዎች ነው፡፡ የጦርነት ሂደቱም «ሀብታም ለሀብታም ይጠቃቀሱ ፤ ድሃ ለድሃ ይለቃቀሱ» እንደሚሉት ነው፡፡

በታሪክ ከዚህ የተለየ የጦርነት ሂደት አላየንም፡፡ ጦርነት ሲጀምር ከሀብታሞች ጅምላ ጨራሽ መሳሪያ ይሸመታል፡፡ ሲያልቅ ደግሞ ፖለቲከኛ ተጠቃቅሶ ይስማማል፤ይተቃቀፋል፡፡ ድሀ ግን ልጆቹን በጦርነት ተነጥቆ እንዲያለቀስ ይፈረድበታል፡፡ የጦርነት መጀመሪያው እና መጨረሻው ይኸው ነው፡፡

ይህ አካሄድ ፈጽሞ ትክክል አይደለም። የዴሞክራሲ ባህልን በመገንባት የአስተሳሰብ ለውጥ በማምጣት ፖለቲካችን «ከኔትወርኪንግ» እና ከኢመደበኛ አደረጃጃት አውጥተን ተቋማዊ ማድረግ ይኖርብናል፡፡ ፖለቲካችን በመርህ ላይ የተመሰረተ መሆን አለበት፡፡ ፖለቲካችን ማንኛውም ፖለቲካዊ ጉዳይ በጠረጴዛ ዙሪያ ላይ ተነጋግረን መፍታት እንችላለን ወደሚል መምጣት አለበት፡፡ ከመጠፋፋት እሳቤ መውጣት አለበት፡፡

የተለያየ ሃሳብ የያዙ አካላት ለአንድ ሀገር እንደሚሰሩ አምነው የተሻለ ሃሳብ ማምጣት እንጂ ፖለቲካን በብሔር እሳቤ መግዛት፣ የሀሰት ወሬ እና ትርክትን በመገንባት ወይም በአፈሙዝ የበላይነት ማመን ትክክል አይደለም፡፡

በሥራ አጋጣሚ በተለያዩ የሀገራችን ክፍሎች የሚገኙ ክልሎችን አይቻለሁ፡፡ በሄድኩባቸው ክልሎች ሁሉ ከላይ እስከታች የሚገኙ የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች የሥራ አጥ ቁጥርን ለመቀነስ የሚያደርጉት እርብርብ፣ በከተማ እና የገጠር ቀበሌዎች እየተከናወኑ ያሉ የሌማት ቱርፋት ተግባራት እጅጉን የሚበረታቱ እና የበርካታ ወገኖችን ህይወት መቀየር የቻሉ ናቸው ፡፡

የሥራ አጥ ቁጥሩን ከመቀነስ ባሻገር የኑሮ ውድነቱን ከማረጋጋት አንጻር ያላቸውን አስተዋጽኦ ለማመን የሚከብድ ነው፡፡ ይህን እንዲሁ ለማለት ሳይሆን በተግባር ካየሁት ነው፡፡ እነዚህን ሥራዎች ክልሎች ሲያከናውኑ ብዙ የሀብት ወጪ አላደረጉም፡፡ ምክንያቱም ኢትዮጵያዊያን ያልተነካ የምቅ ሀብት ባለቤቶች ናቸው ፡፡

አሁን ላይ በክልሎች የሚታዩት የልማት ስራዎች ኢትዮጵያዊያን ባላቸው እምቅ ሀብት ላይ ትንሽ እሴት መጨመር ከቻሉ ዓለምን ጉድ የሚያስብል ለውጥ ማምጣት እንደሚችሉ ሁነኛ ማሳያ ይመስለኛል፡፡ አሁን ላይ እኛ የምንፈልገው ባለን እምቅ የተፈጥሮ ሀብት ላይ ትንሽ እሴት ጨምሮ ችግርን የሚያጠፋ ለጨለማ ጊዜ መብራት መሆን የሚችሉ ለችግር ጊዜ ብልሃት የሚቀምሩ ፖለቲከኞችን ነው፡፡

እነዚህ ፖለቲከኞች በተግባር የታሪካዊ ቁስ አካል (historical materialism) ሳይንሳዊ ፍልስፍና በውል የተረዱ፣ ስለአንድ ህዝብ ማህበረሰባዊ አስተደዳግ ፣ ህግ እና ታሪካዊ አመጣጥ የተገነዘቡ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

ሁሌም ሰላም እንዲኖር ሁላችንም አበክረን መስራት ይኖርብናል፡፡ በየትኛውም ሁኔታ ሰላም ለሁሉም ነገር ቅደመ ሁኔታ እንጂ ለሰላም ምንም ቅድመ ሁኔታ ማበጀት የለብንም፡፡ ከተጣባን ክፉ የጦር አውርድ ደዌ የሚፈውስ መድኃኒት ይስጠን! አሜን፡፡

ኢኮኖሚ

# ግብርና

## የእንስሳት ሀብት ልማት - በኦሮሚያ ክልል

**ማህሌት አብዱል**

ኦሮሚያ ክልል ምቹ የአየር ፀባይና የተፈጥሮ ፀጋ ካላቸው የሀገሪቱ አካባቢዎች በግንባር ቀደምትነት የሚጠቀስ ነው፡፡ ይህም ምቹ ሁኔታ ለተለያዩ እንስሳት ዝርያዎች እርባታ ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንዳለው ይታመናል፡፡ በክልሉ በአሁኑ ወቅት 25 ነጥብ 5 ሚሊዮን የሚጠጉ የዳልጋ ከብቶች፣ 10 ሚሊዮን በጎች እና ስምንት ነጥብ ሁለት ፍየሎች ባለቤት መሆኑን ከክልሉ ግብርና ቢሮ ያገኘነው መረጃ ያመለክታል።እንዲሁም ሶስት ነጥብ ሰባት ሚሊዮን የሚጠጋ የንብ መንጋ ያለ ሲሆን የዓሳ ምርትም 38 ሺ 500 ቶን በየዓመቱ የሚመረቱበት ክልል ነው፡፡

ይህም እንደሀገር ላለው የእንስሳት ሀብት ድርሻ ከፍተኛ እንዲሆን ያደረገው መሆኑን የክልሉ ግብርና ቢሮ ምክትል ኃላፊ አቶ ቶሌራ ደበላ ይናገራሉ፡፡ «በክልላችን ያለው የእንስሳት ሀብት ከምችት ለክልልም ሆነ ለሀገር ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው፤ የምግብና ስነ-ምግብ ዋስትና ለማረጋገጥም ከፍተኛ አስተዋፅኦ እያበረከተ ነው» ይላሉ፡፡ በተጨማሪም የእንስሳት ዘርፉ ከስራ እድል ፈጠራ ረገድ ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንዳለው ያስረዳሉ፡፡

ይህንን ሀብት በተጨባጭ ጥቅም ላይ ከማዋልና የእንስሳት ሀብቱን ምርታማነት ለማጎልበት ቢሮው ከሚሰራቸው ስራዎች መካከል የእንስሳት ዝርያ ማሻሻል ዋነኛው ስራ እንደሆነ ያነሳሉ፡፡ ክልሉ እየተጠናቀቀ ባለው በጀት ዓመት አንድ ሚሊዮን 500 እንስሳት ዝርያ ማሻሻል ስራ ለመስራት አቅዶ፤ እስካሁን በተሰራው ሥራ አንድ ነጥብ አንድ ሚሊዮን 637 ሺ የእንስሳት ዝርያዎችን በማሻሻል ከተያዘው እቅድ በላይ መከወን ችሏል፡፡ በተጨማሪም 250 ሺ 590 ጥጆች ይወለዳሉ ተብሎ በእቅዱ ተይዞ የነበረ ሲሆን እስካሁን ድረስ ወደ 300 ሺ ጥጆች መወለዳቸውን አቶ ቶሌራ ያስረዳሉ፡፡

«ይህም ከእቅዳችን አንፃር 120 በመቶ ማሳካት መቻሉን ያሳያል፤ በሌላ በኩል የዝርያ ማሻሻል ስራው ክልሉ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ በሠራው ሥራ የተገኘ ውጤት ነው» ይላሉ፡፡ ይህም ይሳካ ዘንድ የአቅም ግንባታ ስልጠና ለባለሙያዎች መሰጠቱን ጠቅሰው፤ በዋናነትም ለእንስሳት አዳቃይ ቴክኒሻኖች ልዩ ትኩረት በመስጠት ስልጠና መሰጠቱን ነው የሚጠቁሙት፡፡ አርሶ አደሮችም በዚህ ዙሪያ ግንዛቤ እንዲጨብጡ ተደርጓል፡፡

«ይህንን ስራ ስንሰራ ቶሎ ከብቶቹ ፍላጎት እንዲያሳዩ የሚያደርግ ቴክኖሎጂ በመጠቀም ነው እንዲዳቀሉ የተደረገው» የሚሉት ምክትል ኃላፊው፤ እንደክልል በተቀመጠው አቅጣጫ መሰረት 'አንድ አመት እንደ አምስት አመት አምስት እንደ 25 ዓመት' በሚለው መርሀ ግብር አማካኝነት አሰራርን የማዘመንና ምርታማነትን ከጊዜው ቀድሞ የመከወን፤ የማሳካት ሂደት መከተሉን ያመለክታሉ፡፡ ይህም ሲባል በአምስት ዓመት የታቀደውን እቅድ በአንድ አመት ማከናወን የሚቻልበት ሂደት መኖሩን ነው ያስረዱት፡፡ በዚህም ክልሉ ካለው ስፋትና የህዝብ ቁጥር አንፃር እቅዱን ለማሳካት ርብርብ መደረጉንም ይጠቁማሉ፡፡

ለዚህም አብነት አድርገው ሲጠቅሱ «በአምስት ዓመት ውስጥ አንድ ሚሊዮን የሚደርሱ ከብቶች ላይ የዝርያ ማሻሻያ ስራ እንሰራለን ብለን አቅደን የነበረ ቢሆንም ዘንድሮ እንደክልል በተቀመጣው አቅጣጫ መሰረት በአመት ውስጥ ብቻ አንድ ነጥብ አምስት ሚሊዮን ከብቶች ላይ የዝርያ ማሻሻል ስራ ሰርተናል» በማለት ነው፡፡

በሌላ በኩል የክልሉ ሰፊ አካባቢ ቆላማና አርብቶ አደር የሚበዛበትና ድርቅ የሚያጠቃው እንደመሆኑ በተጨባጭ ምን ያህል ውጤት መጥቷል ማለት ይቻላል? ተብለው የተጠየቁት ምክትል ኃላፊው ተጠይቀው «ቆላማ የኦሮሚያ ክልል አካባቢ ድርቅ ያጠቃዋል፤ በተለይ ባለፉት ሶስት ዓመታት ከፍተኛ ችግር ነበር፤ ይህንን ችግር ለመፍታት እንደክልል በተቀመጠ አቅጣጫ መሰረት ድርቅን የመከላከልና የመቋቋም አቅም ለማሳደግ ርብርብ ስናደርግ ቆይተናል» ይላሉ፡፡

በተለይም የውሃ ማቆር ስራ ቆላም በመሆኑ አካባቢዎች በስፋት መሰራቱን ይጠቅሳሉ፡፡ በተመሳሳይ የውሃ ፕሮጀክቶችን በማቀናጀት ለሁሉም አርብቶ አደሮች ተደራሽ እንዲሆን ርብርብ መደረጉን ያስረዳሉ። ከዚሁ ጎን ለጎንም የመኖ ልማትን በማጠናከር በድርቅ የሚጎዱትን እንስሳቶች ቁጥር መቀነስ መቻሉንም



የግብርና ቢሮ ምክትል ኃላፊ አቶ ቶሌራ ደበላ፣

> እየተጠናቀቀ ባለው በጀት ዓመት አንድ ሚሊዮን 500 እንስሳት ዝርያ ማሻሻል ስራ ለመስራት አቅዶ፣ እስካሁን በተሰራው ሥራ አንድ ነጥብ አንድ ሚሊዮን 637 ሺ የእንስሳት ዝርያዎችን በማሻሻል ከተያዘው እቅድ በላይ መከወን ችሏል

ያመለክታሉ፡፡ በዝርያ ማሻሻል ረገድም ቆላማ አካባቢ በተለየ መልኩ ሲሰራ መቆየቱን አቶ ቶሌራ አስታውሰው፤ የተለያዩ ትላልቅ መጋዘኖችን በመስራትና የመኖ ክምችት እንዲኖር በማድረግ የነበረውን ችግር ለመፍታት ጥረት ተደርጓል ሲሉ ይናገራሉ፡፡

«ይህም አንደኛ በቆላማ አካባቢዎች ላይ የግጦሽ መሬት ማሻሻያ ሥራ የተሰራ ሲሆን በተለይ አላስፈላጊ የሆኑ እፅዋቶችን እያፀዱ የተሻሻሉ የመኖ ዝርያዎችን ለማስፋፋት ጥረት ተደርጓል» ይላሉ አቶ ቶሌራ፤ ይህም ስራ በዘመቻ መልክ የተከናወነ በመሆኑ ከዚህ ቀደም በቆላማ አካባቢ የሚስተዋለውን የመኖ እጥረት ከፍተኛ በሚባል ደረጃ ማሻሻል መቻሉን ነው የሚያመለክቱት። «ቦረና፣ ምሥራቅ ኦሮሚያ ላይ አላስፈላጊ እፅዋቶችን የማስወገዱ ሥራ በዘመቻ መልኩ በመሰራቱ ከፍተኛ ለውጥ አለ፤ የተለያዩ የመስኖ ዝርያዎችን በማሰራጨት ወደ ልማት የተገባ ሲሆን በአሁኑ ወቅት በጥሩ ሁኔታ ይገኛል» ብለዋል፡፡

እንደ ሀገር የዘርፉን ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ ሰፊ ጥረት እየተደረገ የመሆኑን ያህል ለአርሶና አርብቶ አደሩ የገበያ ትስስር በመፍጠር ረገድ ሰፊ ክፍተት መኖሩ ይታወቃል፡፡ በዚህ ረገድ የኦሮሚያ ክልል ተሞክሮ ምን ይመስላል? በተለይ የተመረቱ የእንስሳት ተዋፅኦ ምርቶችን በቀጥታ ወደ ተጠቃሚው ለማድረስና አምራቹ ኃይል የልፋቱን ዋጋ እንዲያገኝ በማድረግ ረገድ ስለተደረገው ጥረት አቶ ቶሌራን ጠይቀናል። እንደእርሳቸው ማብራሪያ ከሆነ፤ በክልሉ ከመደበኛ የግብርና ስራ በተጨማሪ በሌማት ቱሩፋት መርሀ ግብርም ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ ጥረት ተደርጓል፡፡

ከእነዚህም መካከል የወተት ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ ሲሆን እንደ ክልል ሶስት ነጥብ ሶስት ቢሊዮን ሊትር ወተት የማምረት አቅም መጎልበቱን ያብራራሉ፡ ፡ በመጠናቀቅ ላይ ባለው በጀት ዓመትም የሰኔ ወርን ሳይጨምር ሶስት ነጥብ ሁለት ቢሊዮን ሊትር ወተት መመረቱን ጠቁመዋል፡፡ ይህም ከተያዘው እቅድ አንፃር 92 በመቶ ማሳካት መቻሉን ያመላክታል፡፡

በበጀት ዓመቱ በዶሮ እርባታ ረገድ እንደ ክልል 20 ሚሊዮን የዶሮ ጫጩት ለማሰራጨት ታቅዶ እንደነበር አቶ ቶሌራ አመልክተው፤ በተደረገው ቅስቀሳና ግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ በገጠር የክልሉ አካባቢዎች ብቻ ሳይሆን በከተሞችም ጭምር ያሉ ነዋሪዎች በዘርፉ በመሰማራታቸው 42 ሚሊዮን ዶሮ ማሰራጨት መቻሉን ያስረዳሉ፡፡ በዚህ ምክንያት ምርት በመጨመሩ የእንቁላል ዋጋም ቀላል በማይባል ሁኔታ ቅናሽ ማሳየቱን ያብራራሉ፡፡ ይህም የክልሉን የግብርና ውጤቶች ላይ ይታይ የነበረውን የዋጋ ንረት ለማረጋጋት እንዳስቻለም ይጠቅሳሉ፡፡

እንደምክትል ኃላፊው ማብራሪያ፤ በበጀት ዓመቱ ክልሉ የማር ምርትን ለማሳደግም ሰፊ ርብርብ ሲደረግ ቆይቷል፡፡ በተለይም በሌማት ትሩፋት መርሀ ግብር አማካኝነት አንድ ሚሊዮን የሚጠጋ ዘመናዊ ቀፎ ለማሰራጨት ታቅዶ የነበረ ሲሆን እስካሁን ድረስ 971 ሺ ዘመናዊ ቀፎ ለአርሶ አደሮች እና ለአርብቶ አደሮች ተሰራጭቷል፡ ይህም የእቅዱን 97 በመቶ ያህሉን ማከናወን መቻሉን ያመላክታል፡፡ በዚህ መሰረት የማር ምርትም በዓመት 113ሺ221 ቶን ለማግኘት ታቅዶ የነበረ ሲሆን 117 ሺ 800 ቶን ማር ማምረት ተችሏል፡፡

ከዚህ አንፃር ከእቅድ በላይ ማሳካት የተቻለው አመራሩና ባለሙያው በቅንጅትና በንቅናቄ በመስራታቸው እንደሆነ ምክትል ኃላፊው ያስረዳሉ። «ይህንን ስራ ስንሰራ በሞቢላይዜሽንና የንቅናቄ መድረኮችን አዘጋጅተን በየተዋረዱ ተናበን በመንቀሳቀሳችን ነው ማሳካት የቻልነው» ይላሉ፡፡ በተጨማሪም በበጀት ዓመቱ በልዩ ትኩረት የዓሳ እርባታ መርሀ ግብር እንደክልል ተቀርፆ መሰራቱን አቶ ቶሌራ አመልክተው፤ በዋናነትም አርሶአደሩ በጓሮው ኩሬ ቆፍሮ ዓሳን የማርባት ባህል እንዲስፋፋ መደረጉን ይጠቅሳሉ። ከዚህ ቀደም ዓሳ በማይታወቅባቸው አካባቢዎች ላይ ባሉ በተለያዩ የውሃ አካላት ዓሳ እንዲራባ መደረጉን ነው ያብራሩት፡፡

በበጀት ዓመቱ በተለይም ከእንስሳት ሀብት ልማት ጋር ተያይዞ ያጋጠሙ ችግሮችንና የታዩ ክፍተቶችን በሚመለከት «በተለይም የእንስሳት ዝርያ ማሻሻል ስራ በበቂ ሁኔታ ያለመከናወኑ ተጠቃሽ ነው፡፡ የተሻሻሉ ዝርያ ያላቸው የእንስሳት መጠን አሁን ካለበት በላይ ማሳደግ ይጠበቅብን ነበር» ሲሉ አቶ ቶሌራ ይናገራሉ። የመኖ ልማትም እንዲሁ በክልሉ ካሉ የእንስሳት ሀብት ጋር ሲነፃፀር ተመጣጣኝ ያለመሆኑን ያስረዳሉ፡፡ የመኖ አቅርቦቱን ለማሻሻልም የክልሉ መንግሥት በኢኒሼቲቭ መልክ እየሰራ እንደሆነ ይጠቁማሉ፡፡

የእንስሳት ጤና ሽፋን በበቂ ያለማዳረስም ጎልተው ከታዩ ችግሮች መካከል እንደሚጠቀስም ምክትል ኃላፊው ይናገራሉ፡፡ ዘመናዊ የእንስሳት ቴክኖሎጂ ለአርብቶ አደሩና አርሶ አደሩ በጊዜውና በበቂ ሁኔታ ያለማሰራጨት ሁኔታ ሌላው እንደክፍተት የታየ ጉዳይ እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡ የክልሉ መንግሥት የተለዩ ችግሮችን በቀጣይ በጀት ዓመትም ችግር ሆነው እንዳይቀጥሉ ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ መሆኑን ያመለክታሉ፡፡ ለአብነትም «ዝርያ ማሻሻል ላይ ከአንድ ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ወደ ሁለት ነጥብ አምስት ሚሊዮን ከፍ ለማድረግ ታቅዷል» በማለት ይጠቅሳሉ፡፡ የመኖ ልማትም አሁን ካለው መጠን በእጥፍ ለማሳደግ በሁሉም የክልሉ አካባቢዎች ርብርብ የሚደረግ ስለመሆኑ ያስገነዝባሉ፡፡

የቴክኖሎጂ አቅርቦት ችግሩን ለመፍታትም ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ጋር ለመነጋገር ለመፍታት መታቀዱን አቶ ቶሌራ ይናገራሉ፡፡ « መንግሥት ብቻውን እነዚህን ችግሮች መፍታት የማይችል በመሆኑ ከባለድርሻ አካላት ጋር ያለንን ግንኙነት በማጠናከር፤ በመናበብና በማሳተፍ የምንሰራ ይሆናል» ሲሉ ያስረዳሉ፡፡

እንደ ምክትል ኃላፊው ማብራሪያ፤ በኦሮሚያ ክልል በ2017 በጀት ዓመት በዘርፉ ለመከናወን ከታያዙ ዋና ዋና እቅዶች መካከል የእንስሳት ዝርያ ማሻሻል ሥራ ተጠቃሽ ነው፡፡ ይህንንም ሥራ በስፋት ለማከናወን ያስችል ዘንድ ከዞን ጀምሮ እስከ አርብቶ አደርና አርሶ አደር ድረስ እቅዱ ወርዶ መግባባት ተፈጥሮ የሚሰራ ይሆናል፡፡ ከእንስሳት ጤና አገልግሎት ሽፋን አኳያም በዋናነት ለሁሉም እንስሳት የክትባት አገልግሎት መስጠት ዝግጅት እየተደረገ ነው፡፡ በጥቅሉ በክልሉ የእንስሳት ሀብት ልማትን በቴክኖሎጂ በመደገፍ አርሶ አደሩና አርብቶ አደሩን ተጠቃሚ ለማድረግ እየተሰራ ነው፡፡

ማህበራዊ

# አስኳላ

# የትምህርት ጥራትን የማስጠበቅ እርምጃው ተጠናክሮ ሲቀጥል

ግርማ መንግሥቴ

ከትምህርት ጋር በተያያዘ ካሉ ቁልፍ ቃላት (ጽንሰ-ሃሳቦች) መካከል ሁለቱን የሚያክል የለም። በዓለም አቀፍ ሰብአዊ መብቶችም ሆነ ዩኔስኮ፤ በተባበሩት መንግሥታትም ይሁን በሌሎች ገዥ ዓለም አቀፍ ሰነዶች ውስጥ ሁነኛ ስፍራን የያዘ እንደ ሁለቱ ማንም የለም። በሀገራትም ይሁን መንግሥታት፣ በምሁራንም ይሁን ፖለቲከኞች ስለ ትምህርት ካነሱ ሁለቱን በምንም መልኩ ሊያልፏቸው አይቻላቸውም። በመሆኑም፣ ሁለቱ አንድም ሁለትም ናቸው ማለት ይቻላል። የዚህ ምክንያቱ ደግሞ ተደራሽነት በሌለበት ጥራት ስለማይኖር፣ ወይም ስለ ጥራት ማንሳት ስለማይቻል፤ እንዲሁም፣ ተደራሽነት ብቻ ጥራትን ስለማያመጣ ነው።

የትምህርት ተደራሽነትና ጥራትን በተመለከተ እንደ እኛ ሀገር አብዝቶ የተጨነቀ ያለ እስከማይመስል ድረስ በጉዳዩ ላይ የተብሰለሰለ ሀገርም ሆነ ሕዝብ የለም ማለት ይቻላል። ሁሉም በሚባል ደረጃ በተደራሽነቱም ሆነ ጥራቱ ላይ የሚችለውን ሁሉ ብሏል። በተቃውሞ ጎራም በመሰላለፍ ያልተከራከረ የለም። "መጀመሪያ ተደራሽነት ነው፤ ጥራት ቀጥሎ የሚመጣ ነው"፤ "አይ፣ ጥራት ከሌለ ትውልድ አለቀለት ማለት ስለሆነ ተደራሽነት ያለ ጥራት ዋጋ የለውም" እየተባባለ ሁሉ የመጀመሪያውን ሁለተኛ ሁለተኛውን የመጀመሪያ በማድረግ እሰጥ-አገባው ጣራ ነክቶ እንደ ነበር የሚዘነጋ አይደለም። ነገር አለሙ ሁሉ ተበለሻሽቶ ከነጥብ በኋላ ያለን ዲጂት ማንበብ የማይችል የአካውንቲንግ ምሩቅ አጋጥሞ እንደ ነበር በከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች ሳይቀር ሲነገር ነበር።

የትምህርት ጥራት እንጦሮጦስ የመውረዱ ጉዳይ "ሀ" ብሎ የጀመረው ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ከ40 በላይ መምህራን በ"ችሎታ ማነስ፣ የተባረሩ እለት ነው ከሚሉ ወገኖች ጀምሮ እታች ድረስ ተማሪና አስተማሪ ስፍራ እንዲለዋወጡ እስከ ማድረግ የተወረደ ጊዜ ነው የትምህርት ነገር በኢትዮጵያ በአፍጢሙ የተደፋው የሚል ከ"አዲሱ የትምህርት ፖሊሲ" በተቃርኖ የቆመ ሙግት ሲሰነዘር የነበረ ቢሆንም (ብዙዎች ሲሉት እንደ ነበረው) የሚሰማ ሊኖር ባለመቻሉ ሀገርና ሕዝብ፤ ከሁሉም በላይ ተመራቂዎችን ዋጋ አስከፍሏል። የስነልቦና ጉዳት ሳይቀር አላደረሰም ማለት አይቻልም።

ለሦስት አሰርት ጥቂት ፈሪ ለሆኑ አመታት ስራ ላይ ውሎ የነበረውን ፖሊሲ በተመለከተ፣ ከትምህርት ሚኒስቴርና ተዛማጅ ተቋማት የሚወጡ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት በ"አዲሱ የትምህርት ፖሊሲ" ማስፈፀሚያ መሳሪያነት ሲካሄድ የነበረው የመማር-ማስተማር ሂደት በችግሮች የተተበተበና ፊደል እንኳን መለየት ያልቻሉ ተማሪዎችን ሲያመርቅ የነበረ ጉደኛ (ዮዲት ጉዲት) ፖሊሲ ነው። "መፃፍና ማንበብ የማይችሉ"፣ "3 ከመቶ ብቻ የማትረክ ውጤት በማምጣት ያለፉ" ወዘተ ተማሪዎችን በማፍራት ነው በ"የተማረ የሰው ኋይል" ሲባል የነበረው።

እንደ እነዚሁ ተቋማት መረጃዎች ከሆነ የትምህርት ስርአቱ በ"አዲሱ የትምህርት ፖሊሲ" ስም ፍዳውን ሲያይና ሀገርና ወገንን ዋጋ ሲያስከፍል ነው የቆየው። በመሆኑም "አዲሱ የትምህርት ፖሊሲ" እና ርዝራዦቹ በሌላ፤ የትምህርት ጥራትን በሚያረጋግጡ ሰነዶች መተካት አለባቸው በሚል ስር ነቀላዊ አካሄድ እየተሰራባቸው ይገኛል።

ችግሩ እያየለ መጥቶ ዛሬ የጥራት ጉዳይ አንገብጋቢ በመሆን እያወዛገበ፤ ብዙዎችንም ተጠያቂ እያደረገ፤ በብዙዎች ላይም እየተወሰደ ያለው እርምጃ ብዙዎችን እያስደሰተ ይገኛል። ለትምህርት ጥራት መጉደል መደላድል ናቸው የተባሉ መመሪያና ደንቦች ሁሉ እየተከለሱና ጥራትን ሊያረጋግጡ ይችላሉ በተባሉ አዳዲስ ደንቦችና መመሪያዎች እየተተኩ ነው። እንደ እነዚሁ የመረጃ ምንጮች ከሆነ ይህ ተጠናክሮ የሚቀጥል አሰራር ነው።

የትምህርት ጥራት መጓደል ለበርካታ አዳዲስ ተቋማትና ባለሙያዎች ብቅ ብቅ ማለት ምክንያት የሆነ



አቶ ዳኛው ገብሩ፣

ሲሆን፣ አንዱም "በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የትምህርትና ስልጠና ጥራት ቁጥጥር ባለስልጣን" እና የተቋሙ ሰራተኞች ናቸው።

በዚህም ሆነ መሰል የትምህርት አመራር ተቋማት ውስጥ የትምህርት ጥራትን ርቆ ከተቀበረበት ለመታደግ የተለያዩ ስራዎች እየተሰሩ መሆናቸውን የሚያመላክቱ መረጃዎች እየወጡ ሲሆን፤ አንዱና ቀዳሚው ኢንስፔክሽን ነው። የአጠቃላይ ትምህርት የኢንስፔክሽን መረጃ ትንተና፤ የአጠቃላይ የትምህርት ጥራት ማረጋገጥ ቡድን እና የመሳሰሉት የስራ ዘርፎች ተፈጥረው በስራ ላይ እንዲገኙ ተደርጓል።

ወደ ሙያዊ ቃላት (ፅንሰ-ሃሳቦች)ም ስንመጣ ያው ሲሆን ለዚህም በግብዓት፣ በሂደትና በውጤት ተቋማት ምን ደረጃ ላይ እንዳሉ የሚለዩበት፣ የደረጃ ምደባ የሚሰጥበት፣ ተቋማቱ ያላቸውን ጠንካራ ጎን እና ክፍተት በግብረ-መልስ የማሳወቅ ስራ የሚሰራበት፤ እና ተቋማት ያላቸውን ክፍተት እንዲሞሉ እና የማልማቱን ተግባር ለሚመለከተው ባለድርሻ አካላት ጭምር እንዲያሳውቁ የሚደረግበት መሆኑ በሚመለከታቸው የተበየነው "ስታንዳርድ ኢንስፔክሽን" አንዱ ማሳያ ነው።

የእውቅና እድሳትና የአዲስ እውቅና ፈቃድ አሰጣጥን በተመለከተ "በተደጋጋሚ የሚፈጸም፤ በየጊዜው ግን አዲስ የሚሆን" በማለት የሚገልጸው ባለስልጣኑ በድረ-ገፁ "ሙያ ብቃት ምዘና ምንድነው?" በማለት ከጠየቀ በኋላ፤

"ምዘና (Assessment):- አንድ ግለሰብ ባንድ በተወሰነ የሙያ መስመር በሚፈለገው ዕውቀት፣ ቴክኒካዊ ክህሎትና አመለካከት አኳያ በተቀናጀ አግባብ በብቃት ያለ መሆኑን ወይም አለመሆኑን ለመዳኘት ሲባል ለዚሁ ዓላማ የተዘጋጁ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎችን (Evidence gathering tools) በመጠቀም መረጃ የመሰብሰብ እና ዳኝነት የመስጠት ሂደትን (Process) የሚያመለክት ጽንሰ-ሃሳብ ነው፡፡በማለት ያሰፈረውንም እዚሁ ላይ መጥቀስ ተገቢ ነው።

እዚህ ድረስ ይህንን ማለት ያስፈለገው የወደቀውን የትምህርት ጥራት መልሶ ለመትከል እየተደረገ ያለውን አጠቃላይ እንቅስቃሴ በተመለከተ ትንሽ ለማለት፤ እንዲሁም፣ ጉዳዩን ወደ ኋላ አስታውሶ ወደ ፊት ለማመላከት ያህል ነው።

ሰሞኑን፣ በመዲናይቱ አዲስ አበባ የከተማው መነጋገሪያ (ቶክ ኦፍ ዘ ታዎን) ሆኖ የሰነበተው የትምህርት ጉዳይ ሲሆን፣ ለዚህ ደግሞ ዋና መነሻ ምክንያቱ ትምህርትና ስልጠና ቁጥጥር ባለ ስልጣን ለ2017 የትምህርት ዘመን የሚቀጥሉና የማይቀጥሉ የትምህርት ተቋማትን ለመግለጽ፤ ማለትም የትምህርት ጊዜ ሰሌዳ /ካላንደር/ የነባር ተማሪዎች ምዝገባ ከሰኔ 24 ጀምሮ የሚካሄድ መሆኑ የሚታወቅ ሲሆን፤ በትምህርትና ስልጠና ጥራት ቁጥጥር ባለስልጣን በ2016 ዓ.ም የእውቅና ፍቃድ እድሳት ከተደረገላቸው የትምህርት ተቋማት ውስጥ በስታንዳርድ ማሟላት/አለማሟላት እና ሥርዓተ ትምህርት ትግበራ በተሻለ የፈጸሙ/ያልፈፀሙ ለ2017 የትምህርት ዘመን የሚቀጥሉና የማይቀጥሉ የትምህርት ተቋማትን ለህብረተቡ ግልጽ በማድረግ ግልጸኝነትን ለመፍጠር (ወላጆች ለ2017 ልጆቻቸውን የት ማስመዝገብና የት አለማስመዝገብ እንዳለባቸው ለይተው እንዲያውቁ) በማሰብ የተሰጠው አስደንጋጭና ያልተጠበቀ ጋዜጣዊ መግለጫ ነው።

በየአመቱ "የጋራ ግልጽነት ለመፍጠር" በሚል መነሻ ከትምህርት ተቋማት ባለቤቶች ጋር መድረክ በማመቻቸት የጋራ ውይይት በሚያደርገው፤ በባለስልጣኑ ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ ዳኛው ገብሩ ሰኔ 10 ቀን 2016 ዓ.ም የተሰጠው መግለጫ ፍሬ ነገር፡-

በ2017 ዓ.ም የትምህርት ዘመን ተማሪዎችን መዝግበው የሚያስተምሩ 1ሺህ 332 ትምህርት ቤቶች የማስተማር ፈቃድ የተሰጣቸው ሲሆን፤ 43 ትምህርት ቤቶች በራሳቸው ጊዜ መቀጠል ስላልቻሉ ፈቃዳቸው ተሰርዟል። 150 ትምህርት ቤቶች ጉዳያቸው በሂደት ላይ በመሆኑ ወደ ፊት የሚገለጽ ይሆናል። 41 ትምህርት ቤቶች የትምህርት ፖሊሲውን ባለመጠበቅና ስታንዳርዱን ባለማሟላታቸው ፍቃዳቸው ተሰርዟል የሚለው ሲሆን፤ ፈቃዳቸው የተሠረዘው የትምህርት ፖሊሲውን ባለመጠበቅና መስፈርቱን ባለማሟላታቸው ምክንያት መሆኑ የተነገረላቸው እነዚህ የትምህርት ተቋማት ከላይኛው በተጨማሪም፣

- ለ2017 የትምህርት ዘመን ባደረገው ቁጥጥር የፖሊሲ ጥሰት የፈጸሙና የትምህርት መመሪያዎችን ያላሟሉ 35 የግል ይዞታ ያላቸው የቅድመ አንደኛ እና አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ላይ እገዳ ተጥሏል፤
- ከእነዚህ ተቋማት መካከልም፣ የካ፣ ልደታ ጉለሌና ንፋስ ስልክ ክፍለ ከተማ የሚገኙ ሲሆን፤ የጊብሰን ትምህርት ቤቶች፣ የቅዱስ ሚካኤል አምስት ትምህርት ቤቶች፣ እንዲሁም የካ አፖሎ ትምህርት ቤት እርምጃው ከተወሰደባቸው መካከል ይገኛሉ፤
- ዕገዳ በተጣለባቸው ትምህርት ቤቶች ይማሩ የነበሩ ተማሪዎች በመኖሪያ አቅራቢያቸው በሚገኙ የግልና የመንግሥት ትምህርት ቤቶች ያለምንም ተጨማሪ ክፍያ እንዲስተናገዱ ይደረጋል፤
- የተዘጉት ትምህርት ቤቶችም የተማሪዎችን የተሟላ ማስረጃ እንዲሰጡ ይደረጋል፤
- የቅዱስ ሚካኤል ትምህርት ቤቶች የስያሜ ለውጥ በማድረግ ለመቀጠል በመጠየቁም ጉዳዩ በመታየት ላይ ይገኛል፤

የባለስልጣኑ ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ ዳኛው ገብሩ መግለጫውን ተከትሎ ከጋዜጠኞች ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች መልስ የሰጡ ሲሆን፤ አንዳንዶቹ ተቋማት በተደጋጋሚ፣ እስከ ከንቲባ ፅህፈት ቤት ድረስ የዘለቀ መድረክ ተፈጥሮላቸው የተወያዩ ሲሆን፤ በተደረገው ውይይት መሰረት ወደ ህጋዊነትና ተገቢ አሰራር መምጣት ያልቻሉ ናቸው። ለዚህም እነ ጊብሰን አካዳሚ በማሳያነት አቅርበዋል።

ባለፈው አመት፣ ዘንድሮ የእውቅና ፈቃድ እድሳት አገልግሎት ለሚሰጣቸው የግል የትምህርት ተቋማት የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረክ ላይ፣ አቶ አድማሱ ደቻሳ የባለስልጣኑ ምክትል ሥራ አስኪያጅና የጥራት ዘርፍ ኃላፊ ናቸው"

ዘንድሮ የእውቅና ፈቃድ እድሳት ለግል ተቋማት ይሰጣል። የግብአት ማዘጋጀት ደግሞ ለእውቅና ፈቃድ ሳይሆን ለተማሪዎች የተሻለ ትምህርት ለመስጠት እንዲያግዝ ተብሎ የሚደረግ ነው። በተዘጋጀው ቼክሊስት መሰረት ሁሉም ተቋማት ሊዘጋጅ ይገባዋል። ሁሉም ተቋም ህጋዊ ሆኖ እንዲቀጥል ያስፈልጋል፡፡ ህጋዊ ባልሆነ መልኩ ግን አንድም ተቋም አይቀጥልም በማለት አስገንዝበው የነበረ ሲሆን፣ የአሁኑ እርምጃም ያንን ታሳቢ ያደረገ ስለ መሆኑ መጠራጠር ባይቻልም በወቅቱ ማሳሰቢያውን ልብ ያላሉ ተቋማት የዘንድሮ ተዘጊዎች ለመሆን መብቃታቸው የዘንድሮው ማሳሰቢያ ለሚቀጥለው ትምህርት ነውና በሚቀጥለው አመት የሚዘጉ የትምህርት ተቋማት አይኖሩ ዘንድ ምኞታችን መሆኑን እየገለፅን ወደ ዘርፉ ኃላፊ ማሳሰቢያ እንመለስ።

እዚህ ጋ አቶ አድማሱ ደቻሳ እንዳሉት ሆኗል ወይም/እና አልሆነም ለማለት አይቻለንም። መሆንና አለመሆኑን ለመወሰን እንቸገር እንጂ አንድ ነገር ማለት የምንችል ሲሆን፣ እሱም የአሁኑ ታጋቾች (የታገዱት) ቢያንስ እንዲህ አይነት ነገር ሊመጣ እንደሚችል መረጃው ነበራቸው ማለት ነው። ወይም፣ "ህጋዊ ባልሆነ መልኩ ግን አንድም ተቋም አይቀጥልም" ተብሎ ተነግሯቸው ነበር። ችግሩ፣ ለትምህርት ጥራት ሲባል የተነገራቸውን ወደ ተግባር መቀየር አለመቻላቸው ነውና ለክፉም ለደጉም በህግ የበላይነት ማመን ተገቢ መሆኑን ከስሩ ማስመር ያስፈልጋል።

በመድረኩ ለግንዛቤ ማስጨበጫ ይሆን ዘንድ የተዘጋጀውን ሰነድ አቅርበው የነበሩት የባለስልጣኑ የእውቅና ፈቃድ እድሳት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አቶ ያሬድ ካሳ ሲሆኑ፤ የእውቅና ፈቃድ የሚሰጠው ተቋማት በቂ ግብአትና አደረጃጀት መፍጠራቸውን ለማረጋገጥ፣ ከስታንዳርድ ጋር በማነፃፀር ያሉባቸውን ክፍተቶች በመለየት ወደ ተሻለ ደረጃ ለማድረስ፣ ለተስተዋሉ ክፍተቶች ግብረ መልስ በመስጠት በቀጣይ መታረማቸውን ለማረጋገጥ፣ የተስተዋሉ ክፍተቶች ላይ ድጋፍና ክትትል ለሚያደርገው ባለድርሻ አካል በማሳወቅ ቀጣይነት ያለው ድጋፍና ክትትል እንዲያገኙ ለማድረግ፣ ከስታንዳርድ በታች የሆኑ ተቋማትን በመለየት የእርምት እርምጃ በመውሰድ ለማህበረሰቡ ለማሳወቅ፣ ዜጎች ጥራቱ በተረጋገጠ የትምህርት ተቋማት የመማር መብታቸውን ለማስጠበቅ መሆኑን አስረድተው ነበር። ይህም የሚያመለክተው በባለ ተቋሟቱ ዘንድ እንዲህ አይነት ጉዳይ ሊመጣ እንደሚችል አስቀድሞ ግንዛቤው ነበር ማለት ነውና አሁንም ለሚቀጥለው አመት ከወዲሁ ቆፍጠን ብሎ ማሰብ እንደሚያስፈልግ ማሳሰብ እንወዳለን።

**ለትምህርት ጥራት ሁሉም ዘብ ይቁም!!!**

# ወቅታዊ

# «የኢትዮጵያ እድገት ማረጋገጫና ቁልፍ ያለው በቴክኒክና ሙያ ዘርፍ ላይ ነው»

- ብሩክ ከድር (ዶ/ር)
የኢፌዴሪ ቴክኒክና ሙያ ስልጠና ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር

ዘላለም ግዛው


ፎቶ፡- አሸናፊ ጉደታ

**ከመጀመሪያ ደረጃ እስከ ዩኒቨርሲቲ ድረስ ትምህርታቸውን የተከታተሉት በአዲስ አበባ ከተማ ነው። የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውን ሰኔ ዘጠኝ በሚባል ትምህርት ቤት፣ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ደግሞ አብዮት ቅርስ ተምረዋል፡፡ የከፍተኛ ትምህርታቸውንም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ያጠናቀቁት በቅርስ አስተዳደር ትምህርት ነው፡፡**

**በቢዝነስ ሥራ አመራርና በዓለም አቀፍ ግንኙነት እስከ ሶስተኛ ዲግሪ ተከታትለዋል፡፡ ደቡብ ክልል ውስጥ ደራዊት በምትባል የገጠር አካባቢ የተወለዱት የዛሬው እንግዳችን ለቤተሰባቸው አራተኛ እና መንታ ሆነው ቤተሰቡን ከተቀላቀሉት አንዱ ናቸው፡፡ መንታ ወንድማቸው ሀገርን በህግ ሙያ በኃላፊነት ሲያገለግሉ እርሳቸው ባለሙያዎችን እያፈራ ያለውን የቴክኒክና ሙያ ስልጠና ኢንስቲትዩት ተቋምን በዋና ዳይሬክተርነት እየመሩ ይገኛሉ፡፡**

**«ድርና ማግ« በሚል ርዕስ በ2011 ዓ.ም ያሳተሙት እና ኢትዮጵያውያንን እርስ በእርስ በሚያስተሳስሩ የጋራ እሴቶች ዙሪያ የሚያጠነጥነው እና በ2008 ዓ.ም የታተመውን በአረቡ ዓለም የተከሰተውን የለውጥ እንቅስቃሴ የሚቃኘውን €€የአረቦችን ጸደይ« መጽሐፎችን ለአንባብያን አበርክተዋል፡፡ የዛሬው እንግዳችን ብሩክ ከድር (ዶ/ር) ፡፡**

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅትም ከእንግዳው ጋር ያደረገው ቃለ መጠይቅ እንደሚከተለው ተጠናክሮ ቀርቧል፡፡ መልካም ንባብ፡፡**

**አዲስ ዘመን፡- ቴክኒክና ሙያ ትምህርት በኢትዮጵያ ያለው ታሪክ ምን ይመስላል (አጀማመሩ፣ ሂደቱ** አሁን እስከደረሰበት) ?

ብሩክ (ዶ/ር)፡- ቴክኒክና ሙያ ትምህርት በኢትዮጵያ ረጅም ታሪክ አለው። በተለይም ከዘመናዊ ኢትዮጵያ ምስረታ ጀምሮ ከወሰድን ዘርፉ የመንግሥት ትኩረት መሆን የጀመረው ዘመናዊ ትምህርት መምጣትን ተከትሎ በ1905 ዓ.ም በወጣው አዋጅ ነው። ይህ አዋጅ ልጆች የአንድ ሙያ ባለቤት ሆነው መውጣት አለባቸው የሚል ድንጋጌን አውጇል። መደበኛ ትምህርት ከታወጀ በኋላ በብዛት የምናገኘው እንደመደበኛ ቴክኒክና ሙያ ስልጠና ከወሰድነው የአሰለጣጠን ሥርዓት የጀመረው ከሚሽነሪዎች መምጣት ጋር ተያይዞ ነው። ሚሽነሪዎች በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች የሙያ ማሰልጠኛ ማእከላት ለመገንባት ጥረት አድርገዋል። ከእዛ በኋላ በነበረውም የጣሊያን የአምስት ዓመታት ጊዜ አንዳንድ የቴክኒክ ስልጠናዎችን የሚሰጡ ተቋማትን እዛም እዚህም ለመገንባት ጥረት ተደርጓል። ከእነርሱ መውጣት ከ1930ዎቹና 40ዎቹ በኋላ በርካታ ተቋማት ለመመስረት ጥረት ተደርጓል።

የቀዳማዊ አጼ ኃይለስላሴ መንግሥት የቴክኒክ እና ሙያን ጉዳይ ጉዳይ ብሎ የያዘበት ወቅት ከተግባረ ዕድ መመስረት ጋር ይያያዛል። ተግባረዕድ 1942 ዓ.ም ሙያን ቴክኒክን ለማሰልጠን በሚል ዓላማ የተቋቋመ ነው። በወቅቱም የአስመራ ቴክኒክ ትምህርት ቤት የሚባልም ነበር። ወደ 1950ዎቹ ስንመጣም የተወሰኑ የቴክኒክና ሙያ ተቋማትን እዛም እዚህም ለማቋቋም ጥረት ተደርጓል።

በ1970ዎቹ ስንመለከትም ደርግ ስልጣን ከያዘ በኋላ በሀገር በቀር ማህበረሰብ ተኮር የስልጠና ተኮር መስኮች ላይ በማተኮር የቴክኒክ ትምህርቶች ይሰጡ ነበር። በኋላ ግን በፖሊሲ መልክ የቴክኒክና ሙያ ዘርፍ በፖሊሲ ግልጽ አቅጣጫ ተቀምጦለት 1986 ዓ.ም የወጣው የኢትዮጵያ ትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ ባግባቡ ትርጉም ሰጥቶታል። ከዛም በኋላ እ.አ.አ 2001 ቴክኒክና ሙያን የሚያስተባብር የሚኒስቴር መስሪያ ቤት በዴኤታ ደረጃ ተሰይሟል። ከእዛ በፊት በፕሮግራሞች፣ በዳይሬክቶሬትና መሰል የነበረው በዴኤታ ደረጃ ጭምር እውቅና ተሰጥቶታል።

በመቀጠልም የቴክኒክና ሙያ አዋጅ፣ ህጎች፣ ፖሊሲ የበለጠ እየተብራራ የወጣበት ሁኔታ ይታያል። የቲቬት ካውንስል የመመስረት ሥራ፣ የትምህርት ፍኖተ ካርታ፣ በሂደትም 2015 ዓ.ም ኢትዮጵያ እየተመራችበት ያለው የትምህርት እና ስልጠና ፖሊሲ ጸድቆ ሥራ ላይ ውሏል። ይህንን ተከትሎም የሥራ እና ክህሎት ሚኒስቴር እንዲቋቋም ተደርጓል። ላለፉት 100 ዓመታት በኢትዮጵያ መንግሥት ትኩረት ሰጥቶት ጉዳዩን ከያዘው በኋላ ያለው እድገት እስካሁን እስከደረስንበት እነዚህን ደረጃዎች ያለፈ ነው፡፡

**አዲስ ዘመን ፡- በተለያዩ የመንግሥት ሥርዓቶች ለቴክኒክና ሙያ ዘርፍ ተሰጥቶት የነበረው ትኩረት እንዴት ይገለጻል?**

**ብሩክ (ዶ/ር)፡-** በተለያዩ የመንግሥታት ሥርዓት ወቅቶች ለቴክኒክና ሙያ ዘርፎች የተለያየ ትኩረት ሲሰጥ ቆይቷል። በየጊዜው በነበሩ የመንግሥት እይታዎች ቴክኒክና ሙያ ዘርፍ የተለያየ የትኩረት ደረጃ ነበረው። ትምህርት ቤቶቹን የመክፈት፣ ስልጠናዎችን የመስጠት ቀደም ሲልም ሙከራዎች ነበሩ። ነገር ግን ለዘርፉ ከፍተኛ ትኩረት የተሰጠው በተለይም ከአምስት ዓመታት ወዲህ ባለው ጊዜ ነው። አሁን ያለው የለውጥ አስተዳደር የቴክኒክና ሙያን ዘርፍ ጎላ ብሎ እንዲታይ ለማድረግ ትልቅ እንቅስቃሴ አድርጓል። ለዚህ ማሳያዎች አሉ። አንዱ ማሳያ ቴክኒክና ሙያን የሚያስተባብር ራሱን የቻለ ሚኒስቴር መስሪያ ቤት ተቋቁሟል። የሥራ እና ክህሎት ሚኒስቴርን እንደሚኒስትሪ ማቋቋም መቻሉ የሚያሳየው ለዘርፉ የተሰጠውን ትኩረት ነው።

በተለያዩ የመንግሥታት ሥርዓቶች ለዘርፉ የተሰጠው ትኩረት እንደተጠበቀ ሆኖ ያመጣቸው ለውጦችም እንዳሉ ሆነው ግን በተለይም አሁን ያለው የለውጥ አስተዳደር ቴክኒክና ሙያን የድህነት መውጫ መንገድ ነው የሚለውን አደረጃጀት ከመፍጠር ጀምሮ የቅርብ ክትትል፣ ድጋፍ እስከ ማድረግ ድረስ ትኩረት እያገኘ ያለ ዘርፍ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ሙያና ሙያተኞች ሀገራዊና ሕዝባዊ ፋይዳቸው እንዴት ይገለጻል፣ ዓለም አቀፍ ተሞክሮውስ ምን ይመስላል ?**

**ብሩክ (ዶ/ር)፡-** የቴክኒክ እና ሙያ ጉዳይን አጥብቀው በያዙ ሀገራት የቴክኖሎጂ ልማት ሥራ ስኬታማ ነው። የድህነት እና የሥራ አጥ ምጣኔ ዝቅተኛ ነው። በዚህ ምክንያትም የዳበረ ኢኮኖሚ ለመገንባት የቻሉ ሀገራት ተፈጥረዋል። ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ተደርጎ የሚወሰደው የጀርመን ነው።

የጀርመን ቴክኒክና ሙያ ረጅም ጊዜ የዳበረ ልምድ ያለው ነው። ዛሬ ላይ ጀርመን ከአምስት በመቶ ያላለፈ ምጣኔ ነው ያላት። ምክንያቱ ደግሞ ቴክኒክና ሙያን ሙጥኝ ብላ በመያዟ ነው። የቴክኒክና ሙያ ሥርዓታቸውም ባለሁለት ሥርዓት በመባል የሚታወቅ ነው። የገነቡት ሥርዓት አንድ ሰው ወደቴክኒክና ሙያ ሲገባ መጀመሪያ የአንድ ኩባንያ ተቀጣሪ ሆኖ የተወሰነ ጊዜውን ደግሞ ትምህርት ቤት ውስጥ የሚያሳልፍበት ነው።

በመሆኑም ኢንዱስትሪዎቻቸው፣ የማሰልጠኛ ተቋማት፣ የመንግሥት ሚና አላቸው። እንደጀርመን ባሉ ሀገራት ሁሉም ተባብረው አንድን ዜጋ ለመቅረጽ ይረባረባሉ። ሲንጋፖርን በአብነት ብናነሳ ቴክኒክና ሙያን በመጠቀሟ ምክንያት የክህሎት ሥራ ላይ በማተኮሯ ምክንያት ባለፉ 40 ዓመታት ከነበረችበት የከፋ ድህነት ወጥታ ምሳሌ መሆን ችላለች። በወቅቱ ሲንጋፖርን ይመራ የነበረው የሲንጋፖር አባት በመባል የሚታወቀው ሊኩዋን የሚባል መሪያቸው ያለን ሀብት የተፈጥሮ ሀብት አይደለም፣ ውሃ ከማሌዥያ በፓይፕ እየቀዳን ነው፣ ሀብታችን የሰው ልጅ ነው ብለው ሰው ላይ በመስራታቸው በቁጥር አምስት ስድስት ሚሊዮን አካባቢ የሚገመት ሕዝብ ከሀገሩ በላይ 15 ሚሊዮን የሚሆኑ የሌሎች ሀገራት ሕዝቦችን አቅፎ የዓለም አራተኛ ሀብታም ሀገር መገንባት የቻሉት ቴክኒክና ሙያ ላይ ስለሰሩ ነው።

ሌላው ዓለም ላይ ያለው የቴክኒክና ሙያ ልምድ ዜጎችን ከድህነት ለማውጣት፣ የቴክኖሎጂ ሥራን ለመሥራትና የበለጸገ ኢኮኖሚ ለመገንባት አቅም መፍጠር የሚችል ዘርፍ ሆኖ አገልግሏል፤ በማገልገልም ላይ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- እንደ ሀገር ስንከተለው በነበረው የትምህርት ፖሊሲ ምክንያት ወደቴክኒክና ሙያ ትምህርት የሚገቡ ተማሪዎች ከ10ኛ ክፍል ወደ መሰናዶ ማለፍ ያልቻሉ ነበሩ። ይህ የፈጠረው አሉታዊ ገጽታ አለ ። ይሄንን ገጽታ ለመቀየር የተሄደበት ርቀት ምን ይመስላል?**

**ብሩክ (ዶ/ር)**፡- የቴክኒክና ሙያ ዘርፍ አንዱ ፈተና የተሳሳተ ምስል በማህበረሰቡ ውስጥ መዳበሩ ነው። ማህበረሰቡ ቴክኒክና ሙያን እንደሁለተኛ አማራጭ ነው የሚያየው። የወደቀ ሰው መሰባሰቢያ አድርጎ ነው የሚመለከተው። ነገር ግን ቴክኒክና ሙያ የዜጎች ሕይወት የሚቀየርበት፣ እጃቸው የሚፍታታበት፣ በቀላሉ ባገኙት ስልጠና ተመስርተው ወደኢኮኖሚ ገብተው ሕይወታቸውን የሚያሻሽሉበት መስክ ነው። መደበኛው ትምህርት የማሰላሰል አቅም ሊጨምር ይችላል፤ ንድፈሃሳባዊ አቅም ሊጨምር ይችላል፤ ያስፈልጋልም።

የቴክኒክና ሙያ ዘርፍ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ዜጎች ክህሎት አግኝተው ወደሚፈለገው የሙያ መስኮች እንዲሰማሩ ማድረግ ያስችላል። ነገር ግን ይህንን መገንዘብ ላይ ገና ባለመሰራቱ ኢትዮጵያ ውስጥ ለሙያ፣ ለቴክኒክ ጉዳይ ያለን ምስል በጣም የተዛባ ነው። በዚህ ምክንያት የአንድን ሙያ ባለቤት ያከበረ እሳቤ አልዳበረም። የብረት ሰራተኛን ቀጥቃጭ ብለን ነው የኖርነው፣ ለሸክላ ሥራ ባለሙያን ስም ሰጥተን ስናንጓጥጥ ከርመናል፣ ማህበረሰባችን አንጥረኛ ቀጥቃጭ ሲል ነው የከረመው።

የእንጨት ሙያን ሰርቶ በእንጨት ጥበብ ሕይወቱን የሚያሻሽልን ሰው ማህበረሰቡ ክብር አይሰጠውም። በሥራ መስክ የተሰማራ አድርጎ አያስበውም። በዚህ ምክንያት ለእነዚህ ሙያዎች የምንሰጠው ምስል የተሳሳተ ነው። ነገር ግን በሌላው ዓለም አንድ አናጺ፣ የኤሌክትሪክ፣ የብረት ባለሙያ የሚያገኘው ከበሬታ ከፍተኛ ነው። የጠነከረ ማህበራዊ ግንኙነት አለው፣ በትዳር ግንኙነትም ተፈላጊ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- አሁን በተሻሻለው የሀገሪቷ ፖሊሲም ወደ ዩኒቨርሲቲ መግባት የሚያስችለውን የመቁረጫ ነጥብ ያላሟሉ ተማሪዎች ናቸው ወደ ዘርፉ እየገቡ ያሉት። ይሄስ ምን ያህል ከቀደመው አካሄድ ተላቋል ማለት ይቻላል?**

**ብሩክ (ዶ/ር)**፡- ከቀደመው አሰራር በተለይ የአሁኑ ትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ ክፍት ያደረጋቸው ጉዳዮች አሉ። ለምሳሌ ቴክኒክና ሙያ ራሱ እስከ ከፍተኛ የአሰለጣጠን ደረጃ እንዲያድግ በሩን ክፍት አድርጎታል። በዚህ መሰረት አሁን ያለው የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ እስከ ስምንት ደረጃ ድረስ አድጓል። ይህ ማለት ዜጎች እስከ ደረጃ አምስት አድቫንስድ ዲፕሎማ ከደረሱ በኋላ ቀደም ሲል ዝግ ነበር። ዝግ የነበረውን ደረጃ የአሁኑ ፖሊሲ ክፍት አድርጎታል። ደረጃ ስድስት በሌላ አጠራር የዲግሪ፣ ደረጃ ሰባት በሌላ አጠራር የማስተርስ ዲግሪ፣ ደረጃ ስምንት ወደ ተርሚናል ወይም የፒኤችዲ ዲግሪ ሆኖ እንዲቀረጽ ተደርጓል። እስከ ከፍተኛው የአሰለጣጠን ደረጃ መድረስ ይቻላል።

ለምሳሌ የፌዴራል ቴክኒክና ሙያ ስልጠና ኢንስቲትዩት ከተሰጡት ስራዎች መካከል አንዱ ከደረጃ ስድስት በላይ የሰለጠኑትን እና ከመላ ሀገሪቱ የተውጣጡትን ያሰለጥናል። የወደቁ ናቸው የሚባለውም ቢሆን 12ኛ ክፍል አጠናቅቀው ዩኒቨርሲቲ የሚገቡ ዜጎች በቀጥታ ይህንን ተቋም መቀላቀል ይችላሉ። እንደውም አንድ ዙር አስመርቀናል። በአሁኑ የገቡም 300 ሰልጣኞች አሉ። እነርሱን ለኢንደስትሪው እያዘጋጀናቸው ነው።

የወደቀ ነው የሚሰባሰብበት የሚባለው ነገር እየተቀረፈ፣ እየተስተካከለ በሩ ዝግ የነበረው ማደጊያ መሰላሉ ክፍት እየሆነ መጥቷል። አምና የዩኒቨርሲቲ የማለፍ ምጣኔ ሶስት በመቶ ገደማ ነበር። በተቃራኒው ግን ቴክኒክና ሙያ ላይ ከሶስት ሚሊዮን ዜጎች በላይ እየተማሩ ይገኛሉ።

እ.አ.አ ከ2011 ጀምሮ በዲግሪ ደረጃ ማስተማር ተጀምሯል። በሁለተኛ ዲግሪም እያስተማርን እንገኛለን። በቀጣይ የፒኤችዲ (የሶስተኛ ዲግሪ) መርሀ ግብር ለመክፈት ቅድመ ዝግጅት ተጠናቅቋል። ሰልጣኞች ከሁሉም ክልሎች ተመልምለው ሰልጥነው ይወጣሉ። በተቋማችን ተምረው የሚወጡ ተማሪዎች የቴክኒክና ሙያ መምህራን ይሆናሉ፤ የቴክኒክና ሙያ አመራር ትምህርት ክፍል የተማሩት ደግሞ መሪዎች ይሆናሉ፣ ለኢንዱስትሪ ግብአት የሚሆኑትም ቴክኒሽያኖች ይሆናሉ። በኢትዮጵያ በሚገኙ 15 ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጆች ማለትም ባህር ዳር ፖሊቴክኒክ፣ ተግባረዕድ፣ ዊንጌት ፖሊቴክኒክ ኮሌጅ፣ ጅግጅጋ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ፣ ኢትዮ ኢጣሊያ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ፣ ድሬዳዋ ፖሊቴክኒክ ኮሌጅ፣ አሰላ ፖሊቴክኒክ ኮሌጅ፣ ሆለታ ፖሊቴክኒክ

ወደ ገጽ 10 ዞሯል

# ወቅታዊ

## «የኢትዮጵያ እድገት ማረጋገጫና ...

ከገጽ 9 የዞረ



ኮሌጅ፣ ውቅሮ፣ አዲግራት፣ ማይጨውና በመሳሰሉት ኮሌጆች እየተተገበረ የሚገኝ ነው።

**አዲስ ዘመን ፡- የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ከገበያ ፍላጎት ጋር የሚስዋወጥ መሆኑ ይታወቃል። ከዚህ አንጻር ስልጠናዎቻችሁ ምን ያህል ገበያ ተኮር ናቸው ?**

**ብሩክ (ዶ/ር) ፡-** የቴክኒክና ሙያ ስልጠና ገበያ መር እና ገበያ ላይ መሰረት ያደረገ የአሰለጣጠን ሥርዓትን መከተል አለበት። ይሄ በመደበኛም በአጫጭር ስልጠናም ነው የሚተገበረው። በመደበኛ ስልጠና እስካሁን የቀረጽናቸው መርሀ ግብሮች የሥርዓተ ትምህርት ክለሳ በየጊዜው ይደረጋል።

አዳዲስ መርሀ ግብሮች ሲከፈቱ በቅርብ ምሳሌ ባነሳልህ ፋሽን ቴክኖሎጂ አዳጊ ዘርፍ ነው። ገበያው ይህንን ዘርፍ ስለሚፈልገው በተቋማችን ከፍተናል። ወደፊት የምንከፍታቸው ዘርፎች አሉ። ገበያውን መሰረት በማድረግ በመደበኛም በአጫጭር የሥልጠና መስኮች ላይም አዳዲስ መርሀ ግብሮች መከፈት ተግባራዊ እየተደረገ ነው። 22 መስኮች በመጀመሪያ ዲግሪ 19 መስኮች ደግሞ በማስተርስ ዲግሪ ይሰጣሉ።

ገበያን መሰረት ባደረገ መንገድ የስልጠና መስኮች ላይ ጥናት ይደረጋል፣ ሥርዓተ ትምህርት ክለሳ ይደረጋል፣ የተከፈቱ አሉ፣ የሚከፈቱም የትምህርት ክፍሎች ይኖራሉ።

**አዲስ ዘመን፡- ቀጣሪ ተቋማትና ባለ ሀብቶች ከዚህ ዘርፍ የሚወጡ ሰልጣኞችን ተቀብሎ የመቅጠርና የማሰራት ፍላጎ ታቸውና ዝግጁነታቸው ዝቅተኛ እንደሆነ ይታወቃል። ይሄንን በአሰራር ለመፍታት የሄዳችሁበት ርቀት ካለ ቢገለጽ?**

**ብሩክ (ዶ/ር) ፡-** በተወሰነ መልኩ እውነትነት አለው። በሀገራችን የግሉ ዘርፍ አጭር ዕድሜ ያለው ነው። ከቴክኒክና ሙያ የሚወጡ ተማሪዎችን ተቀብሎ፣ በተግባር አሰልጥኖ መቅጠር ላይ ልምምዱ መጠንከር አለበት። ነገር ግን የግሉ ዘርፍ ከፍተኛ ቀጣሪ ነው። የመንግሥት የልማት ድርጅቶችም ብዙ ተማሪዎችን ከቴክኒክና ሙያ ተቋማቱ ይቀበላሉ። አንዳንድ መስኮች ለምሳሌ የቱሪዝም ዘርፍ በምረቃ ቀናቸው አብዛኞቹ ተማሪዎች ተቀጥረዋል። አንዳንድ ዘርፍ ደግሞ ከኩባንያዎቹ ጋር ተቀራርበን በመስራት ያሉትን ችግሮች መቅረፍ ይጠበቅብናል፡፡

ሆኖም ኢንዱስትሪው ከቴክኒክና ሙያ ተቋማት የሚወጡትን መቀበል ላይ በየጊዜው መሻሻሎች አሉት። ከተቋማቱ የሚወጡትን ባለሙያዎችን አምኖ ማሽን እንዲያንቀሳቅሱ በማድረግ በቂ አመኔታ ያለመፍጠርም ችግር አለ። ከቦታ ቦታ ልዩነት ስላለው የኩባንያ ባለቤቶች ብቁ ባለሙያዎችን እንዲያፈሩ በማድረግ ረገድ መስራት ያስፈልጋል።

**አዲስ ዘመን፡- የስልጠና ተቋማቱ (ኮሌጆቹ) ምን ያህል በግብአት እና በቴክኖሎጂ የተጠናከሩና ተወዳዳሪ ናቸው ?**

**ብሩክ (ዶ/ር) ፡-** የቴክኒክና ሙያ ዘርፍ ከፍተኛ መዋእለ ንዋይ የሚጠይቅ ዘርፍ ነው። ብዙ ማሽነሪዎች፣ ማሰልጠኛ መሳሪያዎች፣ የአሰልጣኝ አቅምም ይጠይቃል። በዚህ ምክንያት ቴክኒክና ሙያን በገንዘብ የመደገፍ እስትራቴጂ /ቲቬት ፋይናንሲንግ/ የተባለ አምስት አምዶች ያሉት ራሱን የቻለ ፕሮግራም አለ። መንግሥት ለዘርፉ ትልቅ ሚና ስለሚጫወት መዋእለ ንዋይ በማፍሰስ ቴክኒክና ሙያን በገንዘብ መደገፍ አለበት የሚለው ቀዳሚው ነው።

ሁለተኛው ደግሞ ፒፒፒ የሚባለው የፐብሊክ ፕራይቬት ሞዴል ነው፤ የግሉ እና የመንግሥት ዘርፉ ተቀናጅተው ቴክኒክና ሙያን ይደግፉ የሚለው ሲሆን እየተሰራበት ነው። ቲቬት ፈንድ የሚባል ፈንድም ሶስተኛው ነው። በቅርብ አዋጅ ወጥቶለታል።

በተለያየ አግባብ የሚመጡ፣ ዘርፉን ለመደገፍ የሚደረጉ የፋይናንስ ሥርዓቶችን ወደ አንድ መስመር የሚያመጣ ሥርዓት ነው። ሰልጣኙ ራሱ እንዲጋራ ድርሻ እንዲኖረው የሚደረገው በአራተኛ ደረጃ የሚቀመጥ ነው።ራሳቸው ቴክኒክና ሙያ ተቋማቱ ገቢ የሚያመነጩበት እሳቤ ነው፤ የሰው ኃይል አላቸው፣ ማሽን አላቸው ለዚህም ኢንተርፕራይዝ እንዲያቋቁሞ የሚደግፍ ነው። ማሰልጠኛ ተቋማቱ የውስጥ አቅማቸውን አጠናክረው ገቢ ፈጥረው ራሳቸውን መልሰው እንዲደጉሙ ኢንተርፕራይዝ በብዛት ወደመመስረት እየገቡ ነው። ለምሳሌ ቴክኒክና ሙያ ስልጠና ኢንስቲትዩት ቴክኖ ቢዝ የተሰኘ ትልቅ ኢንተርፕራይዝ አቋቁሟል። አላማው ኢንስቲትዩቱ በተወሰኑ ዓመታት ከመንግሥት በጀት ነጻ እንዲሆን ለማድረግ ነው። ብዙ ተቋማት በዚህ ተግባር ላይ ናቸው። አሰላ ፖሊ ቴክኒክን ብትመለከት የውስጥ ገቢ አቅሙን ነው፤ አዲስ አበባ እንደ ተግባረዕድ፣ ዊንጌት ያሉ ተቋማት ጥሩ ልምድ አላቸው። ከመንግሥት በጀት በሂደት ነጻ የሆኑ ተቋማትን ለመገንባት ነው ታሳቢ ተደርጎ እየተሰራ ያለው። ከማሽነሪ፣ ከውስጥ ግብአት አቅም ያነሳኸው በአምስቱ አንኳር እሳቤዎች የሚመራ ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በቴክኖሎጂ ፈጠራ ዘርፉ ምን አስገኘ ?**

**ብሩክ (ዶ/ር) ፡-** ቴክኒክና ሙያ ተቋማት አስደናቂ ከሚያደርጋቸው መካከል አንዱ የቴክኖሎጂ ማሻሻል፣ ፈጠራና ማሸጋገር ላይ ሚና ያላቸው መሆናቸው ነው። ሙከራዎች አሉ። በየተቋማቱ ያሉ መምህራንና ተማሪዎች ለኮርስ ማሟያነት የሚጠቀሟቸው ቴክኖሎጂዎች፣ ማሻሻዎች ፈጠራዎች አሉ። እዛም እዚህም የሚደረጉ ሙከራዎች ግን በሀገር ደረጃ ለውጥ በሚያመጣ መንገድ መሆን አለባቸው፡፡

ለምሳሌ በፌዴራል ደረጃ አንዱ የተደረገው አዲስ እሳቤ ተቋማቱ የቴክኖሎጂ አምራች ማዕከል መሆን አለባቸው በሚል እሳቤ ከሀገር አቀፍ የተውጣጡ ቴክኖሎጂስቶችን ወደ አንድ የማሰባሰብ ሥራ ተሰርቷል። በየጊዜው በሚደረጉ የክህሎት ውድድር የሚያሸንፉ ፈጣሪዎችን ከየኮሌጆቹና በየግላቸው የሚንቀሳቀሱትን በአንድ ማዕቀፍ የማደራጀት ሥርዓት ተዘርግቷል። ለምሳሌ በዚህ ተቋም ከክረምት ጀምሮ 400 በሀገር አቀፍ የተመረጡ፣ያሸነፉና ውድድር ላይ የመጨረሻ የደረሱ የፈጠራ ባለሙያዎችን አሰባስበናል። የቢዝነስ አዘገጃጀት፣ ዲዛይን ማሻሻል፣ የእርስ በእርስ ተግባቦት ስልጠና፣ የቢዝነስ ሃሳብ ፈጠራ ወደተቀራራቢ ሁኔታ ለማምጣት ተሰርቷል።

72 የሚሆኑ የቴክኖሎጂ ፈጠራ ስራዎችን በ11 ክፍል ማለትም፤ በቱሪዝም፣ በኮንስትራክሽን፣ በማዕድን፣ በግብርና፣ በኢነርጂና በመሰል መስኮችን ኩባንያ ሆነው መውጣት የሚያስችል ስራ ተሰርቷል። በአጭር ጊዜ የተሰሩ የቴክኖሎጂ ውጤቶች አሉ። ለምሳሌ ግብርና ላይ መሰረታዊ ለውጥ ማምጣት የሚያስችሉ አነስተኛ በእጅ የሚገፉ ትራክተሮች፣ መስኖ ሥራን የሚያሻሽሉ ሥራዎች የተሠሩ አሉ። በኢነርጂም ዘርፉን የበለጠ ሊያሻሽሉ የሚችሉ እንደባትሪ ምርት የማሻሻል ስራ መመልከት ይቻላል። ማዕድን ላይም የወርቅ ስራ ላይ ድንጋይ የሚፈልጥና ማንጠሪያ ተሰርቷል። የቱሪዝም ዘርፍ ቴክኖሎጂም መንገድ ላይ የሚገፉ የምግብ መሸጫ ጋሪ ተሰርቷል። በአይሲቲ ዘርፍ አይነስውራንን የሚመራ እንጨት፣ የድሮውን ቴክኖሎጂ ያሻሻሉ አሉ። በህክምና ዘርፍም በዘርፉ ማሻሻያ የሰሩ እናገኛለን።

የጎማ ተረፈ ምርትን በመቀየር ታይልስ ማምረት የሚቻልበት አሰራርንም የፈጠሩትን መመልከት ይቻላል። ባለሙያዎቹን ለመደገፍ ከተለያዩ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች ፈጠራውን ጎብኝተዋል። ዋና ችግር የሆነባቸውን የፋይናንስ ችግር ለመደገፍ ከኢትዮጵያ ልማት ጋር በመሆን በተደረገው ስር 72ቱን የቴክኖሎጂ ፈጠራዎች ለመደገፍ ፕሬዚዳንቱ ሁሉንም ፕሮጀክቶች ጎብኝተው 72 ኩባንያዎች ሆነው እንዲወጡ እናደርጋለን ብለው ቃል ገብተው እየተሰራ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ለስልጠናው ጥራት አንዱ ግብአት የአሰልጣኞች ብቃት ወሳኝ እንደመሆኑ አቅማቸውን ለማሳደግ ምን ታከናውናላችሁ ?**

**ብሩክ (ዶ/ር) ፡-** የአሰልጣኞች አቅም ለማሻሻል ዋና ዋና ስራዎችን እየሰራን ነው። ግብአትን፤ ሂደቱንና ውጤቱን ለማሻሻል ታቅዶ እየተሰራ ነው። የመጀመሪያው ፌዴራል ቴክኒክና ሙያ ኢንስቲትዩት የአሰልጣኞች ማሰልጠኛ ተቋም ነው። ከዚህ የሚወጣ ሰው በመላው ሀገሪቱ ተዟዙሮ አሰልጣኝ ይሆናል። እዚህ ተቋም ውስጥ የምንፈጥረውና የምናፈራው አሰልጣኞችን ነው። ከዚህ የሚወጡ ሰዎች በተለያዩ ሙያ ተቋማት፣ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጆች ውስጥ አሰልጣኝ ይሆናሉ።

ጥራት ያለው ስልጠና እንዲሰጥ የስልጠና ጥራት ሶስት ጉዳዮችን ታሳቢ ማድረግ አለበት፤ ግብአት፣ ሂደት እና የሚወጣው የሰው ኃይል ናቸው። ለዚህም ሲባል ግብአት ማሻሻል ላይ እያተኮርን ነው።

የማሰልጠኛ ግብአቶች በመንግሥት፣ በአጋር አካላት አቅም እያሟላን ነው። በተመረጡ የሥልጠና መስኮች ዘንድሮ እንኳን ከፍተኛ መዋዕለ ንዋይ በማፍሰስ ጥራት ያለው ስልጠና እንዲያገኙ የሚያደርግ ስርቶ ማሳያዎችን አደራጅተናል። በአራተኛ ትውልድ በሚባሉ ዩኒቨርሲቲዎች በተሻለ ደረጃ ሶስተኛ ዲግሪ የያዙ ለመቅጠር ጥረት ተደርጓል። ቴክኖሎጂን ለመማርና ለመቅዳት የውጭ ሀገር ባለሙያዎችን በመቅጠር ጥረት ተደርጓል። በዚህ ምክንያት የአሰልጣኞች ስልጠና ጥሩ ግብአት እንዲያገኝ፣ ሂደቱም ዲጂታላይዜሽንን እንዲያካትት ተሞክሯል። ከሌሎች ልምድ ካላቸው ተቋማት ጋር በመፈራረም አሰልጣኞች ተጨማሪ እውቀት እንዲገበዩ ፣ የውጭ ልምድ በማካተት በሀገራዊ ቅኝት እንዲለውጡ ጥረት ተደርጓል።

**አዲስ ዘመን፡- ከለውጥ በኋላ ዘርፉን ሪፎርም በማድረግ ምን ውጤት ተገኝቷል ?**

**ብሩክ (ዶ/ር)፡-** ዘርፉ ራሱን ችሎ እንዲመራ መደረጉ አንዱ ከለውጡ በኋላ የመጣ ውጤት ነው። ቴክኒክና ሙያን በአዲስ እሳቤ ለመምራት ታስቦ እየተሰራ ነው። ስራና ክህሎት ሚኒስቴር ከያዛቸው የለውጥ እሳቤዎች መካከል ስልጠና መስጫ ተቋማት አላማቸው ከስልጠና በላይ ይሁን በሚል «ከስልጠና በላይ» የሚባል እሳቤ መጥቷል፡፡

የማሰልጠኛ ተቋማቱ ማሰልጠኛ ብቻ ሆነው እንዳይቀሩ መደረግ አለበት፤ የሰዎችን ህይወት የሚቀይሩ ፈጠራዎች መታየት አለባቸው፡፡ ከተቋማቱ፣ የሚወጡ ዜጎችም ኢንተርፕረነር እንዲሆኑ ተብሎ ታሳቢ ተደርጎ እየተሰራ ነው። ኩባንያን መፈልፈያ ለማድረግ አጫጭር ስልጠናዎች ላይ ትኩረት ተደርጓል፡፡

ጸጋን መሰረት ባደረገ መንገድ የማደራጀት ስራ አዲሱ የለውጥ እሳቤ ነው። ለምሳሌ በኢትዮጵያ ከ100 በላይ ፖሊ ቴክኒክ ተቋማት አሉ። እስከ 90 የሚደርሱት ጸጋን መሰረት ባደረገ መንገድ ይደራጁ ተብሎ የስልጠና መስክ ሲከፍቱ የተደረገው ጥናትን መሰረት ባደረገ መንገድ ነው። በጋራ ተቋማቱን የሚያሰባስብ የማሰባሰቢያ ካውንስል መመስረታቸው አንዱ የለውጡ እሳቤ ነው። ዘንድሮ በቂ ልምድ ያላቸው ዜጎች የተሰባሰቡበት የቴክኒክና ሙያ ቲንክ ታንክ ግሩፕ ለመጀመሪያ ጊዜ ተቋቁሟል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- የህግ ማእቀፎቹ ምን ይመስላሉ? ዘርፉን በመደገፍ በኩል አስተጽኦአቸው ምን ይመስላል ?**

**ብሩክ (ዶ/ር) ፡-** በቅርብ ዓመታት ከወጡ የህግ ማዕቀፎች ውስጥ አንዱና ዋነኛ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲው ነው። ፖሊሲው ብዙ ሃሳቦችን አጭቆ ይዟል። ብዙ የዘርፉን ጥያቄዎችንም መልሷል። ሁለተኛው እየተጠናቀቀ የሚገኘው የስትራቴጂ ዝግጅት ነው። በፖሊሲ የተመላከቱ ነገሮች እንዲብራሩ በማድረግ ረገድ ትልቅ እገዛ አለው። ከዘርፉ በርካታ ተዋናዮች መካከል ኩባንያዎችም አሉ። የቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ተቋማት፣ ከፍተኛ ተቋማትና ኢንዱስትሪው የሚመሩበት አዋጅ ወጥቷል። መካከለኛና የአነስተኛ ኢንዱስትሪዎች ከቴክኒክና ሙያ ተቋማት ጋር የሚኖራቸው ግንኙነትን በተመለከተ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ጸድቆ ደጋፊ ፖሊሲው ስራ ላይ ውሏል። እነዚን የህግ ማዕቀፎች ስትመለከታቸው ዘርፉን ለማሻሻል ፋይዳ እንዳላቸው መገንዘብ ይቻላል።

**አዲስ ዘመን፡- የዛሬ 10 አመትስ ዘርፉን የት እንጠብቀው ?**

**ብሩክ (ዶ/ር) ፡-** ኢትዮጵያ ግልጽ የሆነ የ10 ዓመታት ፍኖተ ካርታ አላት። የብልጽግና ፍኖተ ካርታው የስ ሃይል ልማቱ ትልቅ ስፍራ ተሰጥቶታል። የዛሬ 10 ዓመት ኢትዮጵያ ውስጥ በኢኮኖሚ አፍሪካ ውስጥ ሊጠቀሱ ከሚችሉ አገራት መካከል እንሆናለን። ኢኮኖሚያችን ያድጋል፣ ብዙ ዜጎች ተጠቃሚ ይሆናሉ። ከድህነት ይወጣሉ፡፡

ኢንዱስትሪን የማስፋፋት፣ ይበልጥ ኃይል የመጠቀም አቅም ያድጋል፣ ግብርና መር የሆነው ኢኮኖሚ ወደኢንዱስትሪው እየተሸጋገረ የሚሄድበት፣ የአገልግሎት ዘርፉ የድርሻውን የሚያበረክትበት ሁኔታ ይኖረዋል። የተረጋጋ፣ ምሳሌ የምትሆን ሀገር፤ በአፍሪካ በኢኮኖሚያቸው ስማቸው ጎልቶ ከሚነሱ ሀገራት መካከል እንሰለፋለን ተብሎ እየተሰራ ነው።

በፍኖተ ካርታው ላይ ትልቅ ሚና ያለው የሰው ሀብት ልማት ነው። የተገለጹት ሁሉ የሚሳኩት ሰው ላይ በሚደረግ የማልማት ስራ ነው። እንደኛ ነዳጅ የሌለው ሀገር አቅሙ ሰው ነው። ሰው ራሱ ነዳጅ ነው፣ የኢኮኖሚ አቅም ነው። ዘርፉም ይህንን ለማሳካት ትልቅ አቅም አለው።

**አዲስ ዘመን፡- ስነበረን ጥሩ ቆይታ በዝግጅት ክፍሉ ስም አመሰግናለሁ!**

**ብሩክ (ዶ/ር)፡- እኔም ስተሰጠኝ ዕድል አመሰግናለሁ!**

# ፋሽን

## ቴክኒክና ሙያ በፋሽን ኢንዱስትሪው

**ሰሚራ በርሀ**

ባሳለፍነው ሳምንት 14ኛው ከተማ አቀፍ የቴክኒክና ሙያ ሳምንት በተለያዩ ሁነቶች ተከብሮ አልፏል። በዚህ የቴክኒክና ሙያ ሳምንት ከተለያዩ የቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ተቋማት የተውጣጡ ተማሪዎች እና አሰልጣኞች የፈጠራ ሥራዎቻቸውን አሳይተዋል። በተለይም የቴክኖሎጂ ፈጠራዎች፣ የእደ ጥበብ ውጤቶች በስፋት የቀረቡ ሲሆን፤ የፋሽን ሾው ውድድርም ተካሂዷል። እኛም የፋሽን ውድድሩን በመታደም እንደሚከተለው አሰናድተናል።

አቶ ሰለሞን እሸቱ በኮልፌ ኢንዱስትሪያል ኮሌጅ ውስጥ የፋሽን ዲዛይን አሰልጣኝና የትምህርት ክፍሉ ኃላፊ ነው። በ14ተኛው የቴክኒክና ሙያ ሳምንት «ሙያ እና ክህሎት ለልማት በሚል መሪ ቃል» በተዘጋጀው ኤግዚቢሽን ላይ በኮሌጁ የሚገኙ የትምህርት ክፍሉ አሰልጣኞች እና የፋሽንና ዲዛይን ተማሪዎች የየራሳቸውን ሥራ ይዘው ቀርበዋል።

በቴክኒክና ሙያ ሳምንቱ የኮሌጁ የፋሽንና ዲዛይን ትምህርት ክፍል ይዘው የቀረቡትንም ሥራ «ውብ ሀገር ክታቴ» የሚል ስያሜ ሰጥተውታል። ክታቴ የሚለው ቃል ትርጓሜውም ተዘርቶ የነበረን እህል ወይንም ተበታትኖ የነበረን ሰው መሰብሰብ ሲሆን፤ በአሁን ሰዓት እየተደረገ የሚገኘውን የሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ማሳያም ነው። የፋሽን ዲዛይን ስራዎቻቸው እንዲሁ የሀገር ውስጥ ግብዓቶችን በመጠቀም ለሀገር ውስጥ ፍጆታ የሚውሉ አልባሳትን በመድረኩ ይዘው ቀርበዋል።

የኮልፌ ኢንዱስትሪያል ኮሌጅ የተለያዩ ስልጠናዎችን የሚሰጥ ሲሆን፤ የፋሽን ዲዛይን ትምህርትንም ከደረጃ አንድ እስከ ደረጃ አራት ድረስ ስልጠናውን ይሰጣል። በትምህርቱ ወቅት ከስዕል እና ንድፍ ከማውጣት ጀምሮ የሀገር ውስጥ ግብዓቶችን በመጠቀም ስፌት ወይም የተለያዩ ልብሶችን በመስራት የራሳቸውን ዲዛይን እንዲፈጥሩ በማድረግ ተማሪዎችን




የማብቃት ስራን ይሰራል።

የቴክኒክና ሙያ ተቋማት አሁን አሁን እየተስፋፉ የመጡት የፋሽን ትምህርት ቤቶች ሳይፈጠሩ ቀደም ሲልም ነበሩ። በዘርፉም በፋሽን ኢንዱስትሪው ፍላጎቱ ያላቸው ሰዎች የሚሰለጥኑበት ነው። የቴክኒክና ሙያ ተቋማቱ የተለያዩ ሙያዎችን ለማሰልጠን የተዘጋጁ እንደመሆናቸው በተለያዩ የሙያ ዘርፎች ላይ ያተኮሩ ስልጠናዎችን ይሰጣሉ።

የኮልፌ ኢንዱስትሪያል ኮሌጅም ወደዚህ የትምህርት ክፍል መቀላቀል ለሚፈልጉ ተማሪዎች በሩን ክፍት ከማድረግ ባሻገር በተለያየ መንገድ መረጃው ማህበረሰቡ ጋር እንዲደርስ ያደርጋል። የቴክኒክና ሙያ ሳምንትን የመሳሰሉ እና ሌሎች የፋሽን ኢንዱስትሪው ላይ ያተኮሩ ዝግጅቶች ላይም የራሱን ስራ ይዞ ይቀርባል።

በ14ኛው የቴክኒክና ሙያ ሳምንት ላይ የራሳቸውን ስራዎች ይዘው የቀረቡ ሲሆን፤ የቴክኒክና ሙያ ተቋማቱ በተለያዩ የኢትዮጵያ ክፍሎች የሚገኙ የባህል አልባሳት ታሪክን የሚገልጹ የልብስ ዲዛይኖችን ይዘው ቀርበዋል። «የተነሳንበት ሃሳብ ውብ ሀገር ነው። ኢትዮጵያ በጣም ሰፊ ናት በዚህ መድረክ ግን የተወሰኑትን መርጠን የተለያዩ የባህል አልባሳትን ይዘን ቀርበናል» የሚለው አሰልጣኙ፤ እንደዚህ አይነት መድረኮች መዘጋጀታቸው ዘርፉን ከማሳደግ አንጻር ኮሌጁ የሚኖረውን ተደራሽነት ያሰፋል። ከዚህም ባለፈ እየሰራ ያለው ስራ እንዲታወቅ ያስችለዋል ያለው አሰልጣኙ፤ የፋሽን እና ዲዛይን ዘርፍ በቴክኒክና ሙያ ተቋማት ውስጥ መሰጠቱ ያለውን ፋይዳ ሲያስረዳም «ሀገራችን በሽመና እና በተለያዩ በሽመና ፈትል ፣ ጥልፍ የታወቀች ሀገር ናት፤ ምናልባት ዘመናዊ እና ወቅቱን የጠበቀ በማድረግ ክፍተቶች ይኖራሉ። የኛም ልብስ የሚያተኩረው ዘመናዊ በሆነ መንገድ ሲሆን፤ የሀገር ልብሶችን በመስራት በየዕለቱ መለበስ የሚችል እንዲሆን ማድረግ ነው።» በዚህም ተቋሙ በሚሰጣቸው ስልጠናዎች ተጽዕኖ ፈጣሪዎችን ማፍራት መቻሉን አስረድቷል።

ወደ ማሰልጠኛ ተቋሙ መጥተው ስልጠናውን የሚወስዱ የፋሽን እና ዲዛይን ተማሪዎች ትምህርታቸውን ሲጨርሱ በተለያዩ ቦታዎች ላይ የመስራት አልያም ደግሞ የራሳቸውን ድርጅት በመክፈት ወደ ስራ ላይ ይሰማራሉ። በየአመቱ ከፋሽን ኢንዱስትሪው ዘርፍ በተጨማሪ በተለያዩ የትምህርት ክፍሎች ከቴክኒክና ሙያ ተቋማት ቀላል የማይባል ቁጥር ያላቸው ተማሪዎች ስልጠናቸውን ወስደው ይመረቃሉ ወደ ስራም ይሰማራሉ። ነገር ግን የቴክኒክና ሙያ ተቋማት በሀገራችን የሰሩትን ያክል የተመሰገኑ አይደሉም። ሲል አሰልጣኙ ያነሳል። "የተለያዩ ወጣቶች በዚህ ዘርፍ ውስጥ በቴክኒክና ሙያ ተቋማት ገብተው ስልጠና ቢወስዱ ከራሳቸው አልፈው ለሌሎች መትረፍ ይችላሉ። እንዲሁም በፋሽን ኢንዱስትሪው ላይ በግላቸው የተሰማሩ ትምህርት ቤቶች የተለያዩ መድረኮችን የሚያዘጋጁ ሲሆን፤ ኢንዱስትሪው ላይ ያተኮሩ እነዚህን የመሳሰሉ መድረኮች በተደጋጋሚ ቢዘጋጁ ዘርፉን ይበልጥ ለማሳደግ ይረዳል»ሲል ይናገራል።

በ14ተኛው የቴክኒክና ሙያ ሳምንት የኮልፌ ኢንዱስትሪያል ኮሌጅ ስራዎችን ይዘው የቀረቡት የደረጃ ሶስት እና አራት ተማሪዎች ሲሆኑ፤ ኮሌጁ ስልጠናውን በሚሰጥበት ወቅት በሀገራቸው ውስጥ የሚገኙ ሀብቶችን ተጠቅመው እንዲሰሩ ያበረታታል። በማለት ትምህርታቸውን ሲጨርሱ እንደቴክኒክና ሙያ ተቋም የትብብር ስልጠና በሚለው መርሀ ግብር ወደ ውጭ ወጥተው ከገበያው ጋር እንዲተዋወቁ ይደረጋልም ብለዋል።

# ትዝብት/ ማረፊያ

## እንደ ጅብ ችኩል ...

**መልካምሥራ አፈወርቅ**

አሁን ላይ ብዙ ነገሮች የተቀየሩ ይመስላል። ቀድሞ በኑሮ ልማድ ህግና መመሪያ የወጣላቸው ጥቂት እውነታዎች ዛሬ በነበር ተረስተዋል። በእርግጥ ጊዜ ጊዜን በተካው ቁጥር የምንጠብቃቸው ለውጦች አይጠፉም። በሂደት አሮጌው በአዲስ መተካቱ፣ የቀደመው በሚከተለው ታሪክ መቀየሩ ግድ ይላል። አንዳንዴ ግን ያልተገቡ ጉዳዮች እንደዋዛ ህግ ሆነው ሲጸኑ ለምን? ማለት ያስፈልጋል።

ጉዳዬን «ድሮ፣ ድሮ ...» እያልኩ ማስታወስ አልሻም። የማነሳው ርዕስ እምብዛም ዓመታት ባለመሻገሩ አባባሉን መጠቀም አያሻኝም። ከጥቂት ጊዜያት በፊት በተለይም ማህበራዊ ሚዲያ ይሉት ልምድ ከመስፋፋቱ አስቀድሞ ለህግና ልማድ ትኩረት ይሰጥ ነበር ብል እያጋነንኩ አይደለም። ማንም ያለወጉ አሰራርን ጥሶ ቢገኝ ለምን ይባላልና መስመሩን ለማለፍ አይዳፈርም።

ወደዘመናችን የየዕለት ልማድ ልመለስ። አሁን ላይ ማንም ተነስቶ የሰዎችን ስም ቢያጠፋ፣ እንዳሻው አስተያየት ቢጽፍ፣ ምስልና ፎቶግራፍ ለጥፎ መዛበቻ ቢያደርግ የሚገስፁ፣ የሚቃወሙት ምናልባትም በጣት የሚቆጠሩ ብቻ ናቸው።

ይህን ከሚያደርጉት ባሻገር አብዛኞቹ እንደወደቀው ዛፍ ምሳር ለማንሳት የሚጣደፉ ይሆናሉ። እንደውም አንዱ በሰጠው ሃሳብ ተመርኩዘው የማይነቀል ስር የሚመዙት ይበረክታሉ። የአብዛኞቹ አስተያየት በክፉ ከተጀመረ ደግሞ ቀጣዩን ለመረዳት አይቸግርም። የእነሱን ፈለግ ተከታዩ በእጥፍ ይበረክታል።

ይህ አይነቱ አጋጣሚ ሲፈጠር አንዳንዶች ሆን ብለው የተዘጋጁ ይመስላል። ዞር ብሎ ከማስተዋል ይልቅ «በለው እንበለው»ን ይዘው መድረኩን የፍልሚያ ሜዳ ያደርጉታል። ተደገግሞ እንደሚስተዋለው አብዛኞቹ ጉዳዩ ስለተነሳ ብቻ የውስጣቸውን ለመዘርገፍ እንጂ ሃሳቡ ከመነሻው ገብቷቸው አልያም ተቆርቋሪ ሆነው አይደለም።

እንዲህ አይነቱ አጋጣሚ ምንጊዜም ለልማደኞቹ አእምሯዊ ባዶነታቸውን ያጋልጣል፣የወሬ ሱሰኝነታቸውንም ያሳያል። ከምንም በላይ ግን ለሚያልፍ ቀን፣ የማያልፍ ክፉ ታሪክ መከተባቸው የህይወታቸው ማፈሪያ ታሪክ ሆኖ በመዝገባቸው ይከተባል።

እንዲህ አይነቱ አጋጣሚ ማህበራዊ ሚዲያውን በጎ ባልሆነ መንገድ የሚጠቀሙ ሰዎችን ልምድ አመላካች ነው። የዚህ አይነቱ ልማድ መበራከት ደግሞ አስቀድሜ ተለምዷዊ ህጋችን እየተጣሰ ነው ላልኩበት ጉዳይ እንደማሳያ ሊሆን ይችላል።

በቅርቡ አንዲት ወጣት አንድ የቤት መኪናን ከቆመበት አስነስታ ዘርፋ ስለመውሰዷ ወሬው ሲመላለስ ቆይቷል። ጉዳዩ እንዲህ መሆኑ ብቻ አይደለም። መኪናውን ሰርቃለች የተባለችው ሴት ፊቷ ሳይሸፈን፣ ስሟ ሳይደበቅ በየሁሉም ገጽ ውርጅብኝ ስታስተናግድም ነበር።

አሁን ላይ ለምን እንደሚደጋገም ባላውቅም እንዲህ አይነት ታሪኮች በግልጽ እየተለጠፉ ነው። በህግ አግባብ እንደተጠቀሰው ግን ማንም ሰው ክስ ቀርቦበት፣ማስረጃ ተደራጅቶበት፣ ጥፋተኛነቱ ተረጋግጦ በፍረድ ቤት እስካልተወሰነበት ድረስ ወንጀለኛ ነው ሊባል አይችልም። በእርግጥ ይህችው ሴት ቆየት ብሎ ክስ እንደተመሰረተባት ተሰምቷል።

ይህ እንኳን ቀድሞ ቢታወቅ ማንነቷን እያነሱ ለመወቅስ በቂ አይሆንም። ውሎ አድሮ የሚገኘው ውጤት ምን እንደሆነ አይታወቅምና ተጣድፎ ስም ማንሳቱ ተገቢ አይሆንም።

አንድ ሰው በዚህ አይነቱ ድርጊት ተሳትፏል ተብሎ ቢያዝ «ተጠርጣሪው» እየተባለ ይጠራል እንጂ እንደወንጀለኛ በአደባባይ ፊቱ ተጋልጦ ስም ከነአባቱ እየተጠራ «እዩት፣ ፍረዱበት» አይባልም። አሁን ላይ ግን ይህ ይዘነው የቆየነው ተለምዷዊ ህጋችን ተጥሶ በሌላ ታሪክ ተተክቷል። ዛሬ አንድ ሰው ድርጊቱን ይፈጽም፣ አይፈጽም ሳይታወቅ በድንጋይ ሊወግሩት፣ የሚሰለፉ በርካቶች ናቸው። ታሪኩን ከስር ከማጥራትና ቆም ብሎ ከማሰብ ይልቅ ሞራል እየነኩ፣ጾታና ማንነትን እያንቋሸሹ፣ ሰድቦ ለሰዳቢ የሚሰጡ ብዙ ናቸው።

ወዳጆቼ! ይህን ሃሳብ ስሰነዝር ድርጊቱን በትክክል የፈጸሙትን ሰዎች ተግባር እያበረታታሁ አይደለም። እውነታው ቀድሞ አይታወቅም እንጂ በአስነዋሪ ታሪክ የሚያልፉ አጥፊዎች ሁሉ ማንነታቸው ቢጋለጥ በእጅጉ ደስ ይለኛል። እስከዛሬ በዚሁ የማህበራዊ ሚዲያ አማራጮች ብዙ ታሪኮችን አይተናል፣ሰምተናል።

ታሪኮቹ ለሌሎች እስካስተማሩ ድረስ መታየት መሰማታቸው ችግር የለውም። የእኔ ተቃውሞ ግን ጉዳዩ በህግ ሳይረጋገጥ አንዱ ሰው በግል ስልኩ አንስቶ ስለለጠፈው ብቻ ውርጅብኝና ኩነናው ለምን? የሚል ነው። በአንዳንዶች ዘንድ ጥንካሬው ስለሌለ እንጂ እንዳደጉት ሀገራት ተሞክሮ መፍትሄ ቢገኝ እሰዬው ነው።

ከደሙ ንጹህ ሆነው በአጉል ፍረጃ በአደባባይ ስማቸው የጠፋ፣ምስላቸው የተለጠፈ ተጎጂዎች መረጃ ቆጥረው ከሳሾቻቸውን በህግ ፊት ማቆም በቻሉ ነበር። ይህን የሚያደርጉ ጠንካሮች በተበራከቱ ቁጥር ብዙዎች ከተለምዷዊ ስህተታቸው ይመለሳሉ፣ ካልታረመ አንደበታቸውም ይቆጠባሉ። አሁን ላይ በማህበራዊ ሚዲያዎች የሚለጠፉትን መረጃዎች አንዳንዴ ፖሊስ ጭምር ሲጋራው እያስተዋልን ነው።

አሁንም ድርጊቱን የፈጸሙት ተጠያቂነታቸው እንዳለ ሆኖ በጥድፊያ የሚወጡ መረጃዎች ሊታሰቡበት ይገባል። ባይ ነኝ። በተለይ ፖሊስ በራሱ አርማና ባለሙያዎች የተረጋገጡ መሰል መረጃዎችን ማውጣቱ አንባቢው ያለምንም እማኝነት ድርጊቱ ትክክል ነው ብሎ እንዲያምን ያስገድዳል።

እኔ እስከማውቀው በተለይ የፖሊስ መረጃዎች ምንጊዜም ተጠርጣሪነትን የሚያስቀድሙ ናቸው። «ተጠርጣሪ» የተባለው አካል ውሎ አድሮ በህግ ፊት ወንጀለኛነቱ እስካልተረጋገጠ ምስሉም ሆነ ሙሉ ስሙ ገሀድ ሆኖ አይታይም። ቀደም ባሉ ዓመታት በነበሩ ተሞክሮዎች እንዲህ አይነት አጋጣሚዎች ሲከሰቱ የግለሰቦች ምስል ያለአንዳች መደባበቅ በአደባባይ እንዲታይ ይደረግ ነበር።

ተጠርጣሪ ሆነው የቆዩ ሰዎች ውሎ አድሮ ህግ ነጻ ሲያወጣቸው ግን መልሰው የሚመለከተውን አካል በስም ማጥፋት ወንጀል ለመክሰስ መንቀሳቀሳቸው አይቀርም። ግለሰቦቹ ፈጽመውታል ከተባለው ድርጊት ጀርባ የራሳቸው ህይወት አለ። ቤተሰብ፣ ማህበረሰብና ማህበራዊ ህይወት ይሏቸው እውነታዎችም ተጽዕኖ ደርበው መምጣታቸው ግድ ይላል።

ይህን ሀቅ ተሻግሮ ጸንቶ ለመቆም ታዲያ «ከአፍ ከወጣ አፋፍ» ይባል ተለምዶን በቀላሉ መቀልበስ የዋዛ አይሆንም። ህግ ነጻ ቢያወጣቸውም ከሌሎች ጋር እንደትናንቱ ተቀላቅሎ ለመኖር ያለፉበት መንገድ ተጽዕኖው የጎላ ነው።

«ተጠርጣሪ» ሆነው መቆየት ሲገባቸው ማንነታቸው በወንጀለኛነት ተጋልጦ በየሚዲያ ታይቷልና የሞራል ስብራታቸው ይልቃል። እንዲህ አይነቶቹ አጋጣሚዎች ሲደጋገሙና ተጠያቂነቱ ሲበዛ ያለ ህግ ውሳኔ የማንም ሰው ፊት ተጋልጦ እንዳይታይ ሆኖ መተላለፍ ያለበት መረጃ ብቻ ተደራሽ ሲደረግ ቆይቷል።

ይህን እውነት ወደዘመናችን አምጥተን ስናየው ደግሞ ችግሩ በእጥፍ ገዝፎ ይታያል። ዓለም በአንድ መስኮት በሚተያይበት ቅርበት በቀላሉ የሰዎችን ስም በማንሳት፣በገሀድ ምስላቸውን ለጥፎ ያሻውን ለማለት መንገዱ አጭርና ቀላል ነው።

በተለይ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ይህ አይነቱ ሀቅ በግልጽ እየተስተዋለ ነው። አንዳንድ ሰዎች ህይወት አጠፉ፣ ሰረቁ፣ አጭበረበሩ ከመባላቸው አፍታ ምስላቸው ከነሙሉ ስምና ታሪካቸው ገሀድ ይሆናል። አሁንም ድጋሚ እንደምለው የሰዎቹን ድርጊት እያበረታታሁ አይደለም። የእኔ ስጋት ከዚህ ጥድፊያ ጀርባ የሰዎቹ ታሪክ ሀሰትና ስህተት ሆኖ ቢገኝ ማካካሻው ምን ይሆናል እያልኩ ነው።

ለማንኛውም የማህበራዊ ሚዲያ አጠቃቀማችን የሰከነ ቢሆን እንማርበታለን እንጂ አንከስርበትም። በጥድፍያና በወሬ ወዳድነት፣ ቅድሚያውን ለመያዝ የምናደርገው ሩጫ ግን የጅብ ችኩል ቀንድ ይነክሳል ይሉትን ብሂል በራሳችን ላይ ከማስተረት ያለፈ የሚጠቅመን አይሆንም። ቆምብሎ ማሰብ ለራስም፣ ለሌላውም ይበጃልና።

# ዓለም አቀፍ



የአሜሪካ ግዙፍ የጦር መርከብ "ቲወዶር ሩዝቬልት" ደቡብ ኮሪያ ስትደርስ

## ሰሜን ኮሪያ በአሜሪካ መሪነት እየተመሠረተ ያለውን "የእስያ ኔቶ" በዋዛ አልመለከተውም አለች

በጋዜጣው ሪፖርተር

ሰሜን ኮሪያ፤ አሜሪካ ከደቡብ ኮሪያ እና ጃፓን ጋር "የእስያ ኔቶ"ን የመሰለ ወታደራዊ ጥምረት እየመሠረተች ነው ስትል ወቀሰች።

ሶስቱ ሀገራት የጀመሩት ግዙፍ ወታደራዊ ልምምድ ሀገራቱ ትብብራቸው እያደገ መሄዱን አመላካች መሆኑንም ነው የሀገሪቱ ብሄራዊ የቴሌቪዥን ጣቢያ የዘገበው።

አሜሪካ፣ ደቡብ ኮሪያ እና ጃፓን ከሃሙስ ጀምሮ "የነጻነት ጥግ" የሚል ስያሜ የሰጡትን የጋራ ወታደራዊ ልምምድ እያደረጉ ነው።

የአሜሪካን አውሮፕላን ተሸካሚ መርከብ (ቲወዶር ሩዝቬልት)ን ጨምሮ የጦር አውሮፕላኖች እና መርከቦችን ያካተተው የጦር ልምምድ የሩሲያው ፕሬዚዳንት ቭላድሚር ፑቲን በፒዮንግያንግ ጉብኝት ባደረጉ ማግሥት ነው የተጀመረው።

ሶስቱ ሀገራት የሰሜን ኮሪያን የኒዩክሌር ፕሮግራምና የማያቋርጥ የሚሳኤል ሙከራ በጋራ ለማስቆም ባለፈው ዓመት በሜሪላንድ ካምፕ ዴቪድ ስምምነት ከደረሱ በኋላ ትብብራቸው ተጠናክሯል።

የሀገራቱን ወታደራዊ ልምምድ እንደ ጦርነት ዝግጅት የምትቆጥረው ፒዮንግያንግ አሜሪካ መራሹን የሶስትዮሽ ወታደራዊ ጥምረቱን በዋዛ እንደማትመለከተው ነው ያስታወቀችው።

ኬሲኤንኤን ጠቅሶ ሬውተርስ እንዳስነበበው ሰሜን ኮሪያ የኮሪያ ልሳነ ምድር ውጥረትን ያባብሳል ያለችውን የሶስትዮሽ ወታደራዊ ትብብር ለመግታት "ከባድ ርምጃ" እወስዳለሁ ብላለች።

አሜሪካ ደቡብ ኮሪያ እና ጃፓንን የሰሜን አትላንቲክ የጦር ቃልኪዳን ድርጅት (ኔቶ) አካል የማስመሰል ሙከራዋንም ኮንናለች።

ለዚህም ለአብነት ያነሳችው ደቡብ ኮሪያ ወደ ዩክሬን የጦር መሣሪያዎችን እልካለሁ የማለቷን ጉዳይ ነው።

ሴኡል በቅርቡ ወደ ኬቭ የጦር መሣሪያዎችን እንደምትልክ የዛተችው የፒዮንግያንግና ሞስኮ "ጠላትሽ ጠላቴ ነው" ወታደራዊ ትብብር አሳስቦኛል በሚል ነበር።

ፕሬዚዳንት ቭላድሚር ፑቲን እና የሰሜን ኮሪያው መሪ ኪም ጆንግ ኡን የተፈራረሙትን የወታደራዊ ስምምነት ተከትሎ ደቡብ ኮሪያ በሴኡል የሚገኙትን የሩሲያ አምባሳደር መጥራቷ ይታወሳል።

ደቡብ ኮሪያ እና አሜሪካ ፒዮንግያንግ በዩክሬን ጦርነት ጥቅም ላይ የሚውሉ የጦር መሣሪያዎችን ለሩሲያ እንደምትልክ ይገልጻሉ።

ሞስኮ እና ፒዮንግያንግ የሚቀርብባቸውን ወቀሳ ደጋግመው ውድቅ ማድረጋቸው ይታወቃል።

## ሩሲያ 36 የዩክሬን ድሮኖችን መትቼ ጣልኩ አለች

በጋዜጣው ሪፖርተር



የሩሲያ አየር መከላከያ ሥርዓት ዩክሬን ወደ በበርካታ የሩሲያ ግዛቶች ያበረረቻቸውን 36 ድሮኖች መትታ መጣሏን የሩሲያ መከላከያ ሚኒስቴር በትናንትናው እለት አስታውቋል፡፡

15ቱ ድሮኖች ከዩክሬን ጋር በምትዋሰነው የኩርስክ ግዛት ተመትተው የወደቁ ሲሆን ዘጠኙ ደግሞ በርካታ ኪሎ ሜትሮች ርቀው በደቡባዊ ሞስኮ ሌፕሴክ ግዛት መመታታቸውን ሚኒስቴሩ በቴሌግራም ገጹ ገልጿል።

እያንዳንዳቸው አራት ድሮኖች ደግሞ በደቡብ ምዕራብ ሩሲያ በሚገኙት ቮሮኖዝ እና ብሪያንስክ ግዛቶች ተመትተው ሲወድቁ በቅርብ ባሉት ኦርዮል እና ቤልጎሮድ ግዛቶች ደግሞ በእያንዳንዳቸው ሁለት ድሮኖች ወድመዋል፡፡

የሊፕሴክ እና ብሪያንስክ ግዛቶች አስተዳዳሪዎች በጥቃቱ የደረሰ ጉዳት አለመኖሩን በቴሌግራም ገጻቸው አስፍረዋል።

የሩሲያ ባለሥልጣናት በዩክሬን ጥቃት የሚደርሰውን ጉዳት ብዙውን ጊዜ ሙሉ በሙሉ ይፋ አያደርጉም። ኪቭ በሩሲያ ትራንስፖርት፣ ወታደራዊ እና የኃይል መሠረተ ልማቶች ላይ ጥቃት እያደረሰች ያለችው፣ ሞስኮ በፈረንጆቹ የካቲት 2022 ጀምሮ በዩክሬን ግዛት ላይ ለፈጸመችው ጥቃት ምላሽ ለመስጠት ነው።

ሩሲያ በዩክሬን የጀመረችው "ልዩ ወታደራዊ ዘመቻ" አሁንም ቀጥሎ እየተካሄደ ነው። ሩሲያ ከወራት በፊት በምስራቅ ዩክሬን በዶኔስክ ግዛት ወሳኝ የተባለችውን አቭዲቪካ ከተማን እና በርካታ መንደሮችን መቆጣጠር መቻሏ ይታወሳል።

ዩክሬን እነዚህን ቦታዎች ለቃ የወጣችው የምዕራባውያን ወታደራዊ ርዳታዎች በወቅቱ ባለመድረሳቸው ነው የሚል ምክንያት ሰጥታ ነበር።

ሩሲያ፣ ዩክሬን በተከታታይ የከባድ መሣሪያ እና የድሮን ጥቃት የምትሰነዝርባትን በድንበር አካባቢ የምትገኘውን ቤልጎሮድን ለመከላከል በዩክሬኗ ካርኪቭ ግዛት በቅርቡ ያልተጠበቀ ጥቃት ፈጽማለች።

በዚህ ጥቃት ሩሲያ በካርኪብ ግዛት ያሉ በርካታ መንደሮችን ተቆጣጥራለች። ይህን ተከትሎ ምዕራባውያን ሀገራት ዩክሬን በለገሷት መሣሪያዎች ሩሲያ ውስጥ ያለ ኢላማ እንድትመታ ፈቅደውላታል። ሩሲያ ይህን የምዕራባውያንን ውሳኔ "በእሳት መጫወት" ነው ስትል መግለጿ ይታወሳል ሲል የዘገበው አል ዓይን ነው።

# ስፖርት





## የወጣቶች አትሌቲክስ ቻምፒዮና ነገ በሀዋሳ ከተማ ይጀምራል

አስማየሁ ግዛው

12ኛው የኢትዮጵያ ወጣቶች አትሌቲክስ ቻምፒዮና ከነገ ጀምሮ በሲዳማ ክልል ሀዋሳ ከተማ አስተናጋጅነት ለተከታታይ አምስት ቀናቶች ይካሄዳል፡፡ በውድድሩ የሚስተዋለውን የእድሜ ማጭበርበር ለመከላከል የህክምና ምርመራ በማድረግ የቅጣት እርምጃ እንደሚወስድም የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን አስታውቋል፡፡

የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን በየዓመቱ የሚያዘጋጀው ከ20 እና ከ18 ዓመት በታች የወጣቶች አትሌቲክስ ቻምፒዮና ከነገ ሰኔ 25 - ቅዳሜ ሰኔ 29/2016 ዓ.ም በሀዋሳ ከተማ አስተናጋጅነት ይካሄዳል። የሩጫ እና ሜዳ ተግባራትን በማካተት የሚካሄደው ውድድሩ ከክልሎች፣ ከተማ አስተዳደሮች እና ክለቦች የተወጣጡ ታዳጊ አትሌቶች ውድድራቸውን ያካሂዳሉ። የውድድሩ ዓላማም በክለቦች ለሚገኙ ታዳጊና ወጣት አትሌቶች የውድድር እድልን በመፍጠር ሀገርን የሚወክሉ ውጤታማና ተተኪ አትሌቶችን ማፍራት ነው። በተጨማሪም በነሐሴ ወር አጋማሽ በፔሩ ዋና ከተማ ሊማ በሚካሄደው የዓለም ከ20 ዓመት በታች ወጣቶች ቻምፒዮና ላይ ኢትዮጵያን የሚወክሉ አትሌቶች እንደሚመረጡበትም ፌዴሬሽኑ በሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫ አስታውቋል፡፡



አቶ አስፋው ዳኜ፤

በቻምፒዮናው 10 ክልሎች፣ 2 ከተማ አስተዳደሮች፣ 32 ክለቦች እና የማሰልጠኛ ተቋማት ይሳተፋሉ፡፡ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው አትሌቶች የሚካፈሉበት ሲሆን፤ 422 ሴት እና 549 ወንድ በድምሩ 971 አትሌቶች የሚፎካከሩም ይሆናል። ለውድድሩ የሚያስፈልገው ዝግጅትም ተጠናቋል፤ በዚህም ዓለም አቀፍ ስልጠና የወሰዱ እና ብቁ የሆኑ 80 ዳኞች ውድድሩን ለመምራት ተመድበዋል። በተጨማሪም የበጎ ፍቃደኛን ጨምሮ ከ150 ሰው በላይ ውድድሩን ለመምራትና ለማስተባበር ተዘጋጅተዋል። ለዚህም በቂ የሆነ በጀት የተመደበ ሲሆን፤ የአስተናጋጁ ክልል አትሌቲክስ ፌዴሬሽን፣ ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ እንዲሁም የጸጥታ ክፍሉ ቅድመ ዝግጅት አድርጓል፡፡ ለውድድሩ አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁሶችም ተሟልተዋል፡፡

በፌዴሬሽኑ የተሳትፎና ውድድር ዳይሬክተር አቶ አስፋው ዳኜ፤ ታዳጊ አትሌቶች በሀገር ውስጥ በለመዱት የአየር ንብረት የውድድር እድል መፍጠር የውድድሩ ዓላማ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ በስልጠና እና ውድድሮች ላይ የቆዩ ታዳጊ አትሌቶችን በሽልማት ማበረታታትና በቀጣይም በዓለም አቀፍ ውድድር ሀገራቸውን እንዲወክሉ ማድረግ ሌላው ተጠቃሽ ነጥብ ነው፡፡ ማንኛውም አትሌት ያለ ትክክለኛ እድሜው የማይወዳደር ከሆነ እርምጃ እንደሚወሰድበትም ዳይሬክተሩ ጠቁመዋል፡፡

የህክምና ክፍሉ ከፍተኛ ባለሙያ ዶክተር አያሌው ጥላሁን በበኩላቸው፤ የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ተገቢና ተተኪ አትሌቶች የሚያስፈልጉት ቢሆንም ከእድሜ ጋር ተያይዞ ችግር እንደገጠመው ጠቁመዋል፡፡ ክለቦች፣ ክልሎች እና አሰልጣኞች፣ አትሌቶችን ያለ እድሜያቸው የሚያወዳድሩ በመሆኑ ከዓለም አቀፉ ተቋምም ጭምር የቅጣት ስጋት ሊፈጥር ችሏል፡፡ የግንዛቤ ማስጨበጫ እንዲሁም እርምጃዎች ተወስደውም መፍትሔ ማምጣት አልተቻለም፡፡ ተተኪን ለማፍራት እና ስፖርቱን ለማሳደግ ሳይሆን ለዋንጫና ለዝና እንደሚሰሩም በርካቶች ይናገራሉ፡፡ ለዚህም ፌዴሬሽኑ በከፍተኛ ደረጃ ትኩረት ሰጥቶ አዲስ የምዝገባና የመረጃ ስርዓትን ለመጀመር ተዘጋጅቷል፡፡ የመጨረሻው የመቆጣጠሪያ ሙከራ በዚህ ውድድር የሚደረግ ሲሆን፤ ሁሉም ክልል እና ከተማ አስተዳደር የእድሜ ምርመራ በማድረግ በህክምና ባለሙያዎች አስፈርሞ እንዲመጣ መደረጉንም ዶክተር አያሌው ገልጸዋል። በውድድሩ በሚገኘው ውጤት መሰረት ሀገራዊ ውሳኔን በማሳለፍ ከዜሮ ለመጀመርም ታቅዷል። በተጨማሪም በፔሩ ሊማ ለሚደረገው የወጣቶች ቻምፒዮና የሚያልፉትን አትሌቶች በህክምና ምርመራ ለመለየት ጥረት ይደረጋል። አሰላ በተካሄደው ከ20 ዓመት በታች ቻምፒዮና 800 የሚደርሱ አትሌቶች እድሜን በማጭበርበራቸው ከውድድር መሰረዛቸውንም ባለሙያው አስታውሰዋል፡፡

አሸናፊ አትሌቶቹን ለማበረታታት ከሜዳሊያ ሽልማት በተጨማሪ እንደየደረጃቸው የገንዘብ ሽልማት የተዘጋጀ ሲሆን፤ ከ1ኛ እስከ 3ኛ የሚወጡ አትሌቶች 1ሺ ብር፣ 800 ብር እና 500 ብር ይሸለማሉ፡፡ በሪሌ ውድድር ከ1-3 የሚወጡት ደግሞ 3 ሺ ብር፣ 2 ሺ ብር እና 1ሺ.500 ብር በቅደም ተከተሉ መሰረት ያገኛሉ። በቡድን ውጤት ቀዳሚ ለሚሆኑት ሶስቱ ቡድኖችም ከ10 ሺ ብር -3 ሺ ብር የገንዘብ ሽልማት ይበረከትላቸዋል፡፡ በድምር የቡድን ውጤት አንደኛ የሚወጣ 15 ሺ ብር፣ ሁለተኛ 10 ሺ ብር እና ሶስተኛ ደረጃን የ8 ሺ ብር ሽልማት የተዘጋጀ ሲሆን ወደ 444 ሺ ብር ለሽልማት ወጪ እንደሚሆን ተጠቁሟል፡፡